ትዕይንት አንድ

መስከረም 19 2007 (መጋረጃ ሲከፈት ሰሎሞን እየገባ ይታያል።)

ሰሎሞን ፡ (ጃኬቱን እያወለቀ) ውህ ገላየን ልታጠብ ነው። መሮኛል መድኃኔዓለምን አስቴር(2) አንቺ አስቴር

[አስቴር ትገባለች]

አስቴር ፡ ምን ብለህ ነው

ስሎሞን ፡ ዉሃ አውጭልኝማ ገላየን ልታጠብ ነው።

አስቴር ፡ አልቋል ።

ሰሎሞን ፡ እና ቅጅልኝ እንጅ ከሌላ (በቁጣ)

አስቴር ፡ አንተ ደግሞ ቁጣህ ከአፍንጫህ ላይ ነው።

ሰሎሞን ፡ አሁን ምን አልኩሽ ተቆጣህ ምትይኝ ዉሃ ቅጅልኝ እኮ ነው ያልኩት

አስቴር ፡ ዉሃይቱ የለችም ። ኧረ እድልህ ተጎማጀህሳ

ሰሎሞን ፡ ለምን አልቀዳሽም? ቅድም ነበረች አይደል ?

አስቴር ፡ እንግዲያ አንተ ማትቀዳ አይተሃት ከነበር ?

ሰሎሞን ፡እህ ስራ እየሄድኩ ረፍዶብኝ አይተሽ አደል ከቤት ቁጭ ብለሽ ስትውይ ብትቀጅ ምን አለበት ?

አስቴር ፡ ቁጭ ብለሽ የምትል ያለስራ የተቀመጥኩ መሰለህ ለራሴ እሳት ሲለበልበኝ ዉሎ ቁጭ ብለሽ ስትውይ ይለኛል ።

ሰሎሞን ፡ እንግዲህ አንቺ አትጨቅጭቂኝ ምሳ አቅርቢልኝ ርቦኛል

አስቴር ፡ ቆይ ገና እየደረሰ ነው

ሰሎሞን ፡ ህ እስካሁን አልሰራሽም

አስቴር ፡ አልሰራሁም አልኩህ እየሰራው ነው እኮ ነው ያልኩህ

ሰሎሞን ፡ እና እሺ አትጨቅጭቂኝ ኧረ እዳ ገባሁ /

አስቴር ፡ ወይ ያደረ ወጥ አለ በዛ ልስጥህ

ሰሎሞን ፡ በቃ ያለዉን ነገር ስጭኝ አሁን ነገር አልፈልግም ።

አስቴር ፡ [እየወጣች] መቼም አንተ ሲሰሩልህም ሳይሰሩልህም ያው ነህ ዉሻ

ሰሎሞን ፡ ዉሻስ ራስሽ ኧረ ይቺ ቅማላም በይ ቶሎ አቅርቢልኝ ውህ ውህ (4)እሾህ ውየ ስመጣ አንዱን ጠቅ ዉዬ ስገባ አንዱን ጠቅ ዉህ በሽተኛ አደረገችኝኮ

[ልጃቸው ቴዎድሮስ ይመጣል]

ቴዲ ፡ አባቴ ደህና ዋልክ

ሰሎሞን ፡ እ ቴዲ መጣህ [ስልክ ይደወልለትና ማዉራት ይጀምራል]

ሄሎ አብርሃም በእዉነት ተገኝልህ ኧረ እንኳን ተገኘ ለመሆኑ ሌባው ተያዘ ምን ያደርጋል ዋናው መገኘቱ ነው ። በል የደስ ደሱን ማታ ተገናኝተን እንጠጣለን ሂሳቡ በእኔ ነው ችግር የለዉም ባክህ በል እሺ ቻው አብርሽየ

[ቴዲ ሲያዳምጥ ቆይቶ]

ቴዲ ፡ምን ተሰርቆ ነው ሰሎሞን ?

ሰሎሞን ፡ ሞባይል[እንደተቆጣ]

ቴዲ ፡ የማን ሞባይል ነው ?

ሰሎሞን ፡ የአብርሃም

ቴዲ ፡ መቼ ነበር የተሰረቀ ?

ሰሎሞን ፡ ትላንት

ቴዲ ፡ ትላንት ተሰርቆ ነው ዛሬ የተገኘ ? [ዝም ይለዋል] ስማርት ስልክ ነው ?

ሰሎሞን ፡ ዉህ አንተ ምን ያደርግልሃል ? ኧረ እድልህ ዞር በል አሁን አትነዝንዘኝ

ቴዲ ፡ ሌቦቹ ተያዙ ? [በዱላ ሊመታው ሲል ውጥቶ ይሮጣል]

ሰሎሞን ፡ የደናና ልጅ [አስቴር እንጀራ እና ወጥ ይዛ ትመጣለች]

[ወጥ ስትጨምር በብሽቀት እያዬ] አስቴር በስነ ስርዓት አድርጊው እንጂ ምንድን ነው ጡብ ጡብ የምታደርጊ ኧረ

አስቴር ፡ እንግዲህ ትበላ እንደሆነ ብላ ምን በሆነ ባልሆነው ይጎማጃል ።

[እየተሳደበ መብላት ይጀምራል]

ቄስ ማሩ ፡ ደህና ዋላችሁ ? ከዚህ ቤት አላችሁ ?

አስቴር ፡ ቄሴ ናቸው ።

ሰሎሞን ፡ ጣ እኒህ ደግሞ ዝምብለው ሁልጊዜ በየወሩ ብር መጠየቅ አይሰለቻቸዉም። በቃ እኔ በጓሮ በር ወጥቼ ልሂድ ሳያዩኝ አንቺ ስጫቸው

አስቴር ፡ እረ እኔ የለኝም

ሰሎሞን ፡ ደመወዝ አውጥተሽ አይደል ?

አስቴር ፡ ወዲያው እኮ ነው ያለቀው ጤፍ ምናምን ገዝቼበት የቀረችኝ መቶ ብር ናት ።

ሰሎሞን ፡ አምሳ ብር አይደል ? ስጫቸውና እኔ በኋላ እሰጥሻለሁ። መቶ ብር ካለሽ እኔ ዛሬ ግብዣ ስላለብኝ ነው።

አስቴር ፡ የሁለት ወር ስለሆነ መቶ ብር ነው። ደግሞ ለቢራ ስንት ታወጣ የለ ? ምን አለበት መቶ ብር ብትሰጥ መቶ ብር ምን አለው ?

ሰሎሞን ፡ ከሰው መሃል ባዶ እጄን ሂጀ ልታዋርጂኝ ነው። ወንድ ልጅ እኮ ነኝ

አስቴር ፡ መቶ ብር ምን ያክል እንዳላጎደለ ነው ?

ቄስ ማሩ ፡ ወለተ ገብርኤል አላችሁ

አስቴር ፡ ደህና ዋሉ ቄሴ ይግቡ

ሰሎሞን ፡ እኔ ልወጣ ነው። በቃ የለም በያቸው

ቄስ ማሩ ፡ ገብረ ሚካኤል አለ ? [የለም እንድትል ያመለክታታል]

አስቴር ፡ አለ ይግቡ [በንዴት ይጮፋል]

ቄስ ማሩ ፡ እንዴት ዋላችሁ [አስቴርን እየባረኩ]

ሰሎሞን ፡ እግዚአብሄር ይመስገን ደህና ዋሉ ? ይቀመጡ [ይባረካል። እንደበሽቀው ይታወቅበታል] ቄስ ማሩ አላስተዋሉትም]]

አስቴር ፡ እዚችጋ ይቀመጡ

ሰሎሞን ፡ በሉ ይጫወቱ እኔ ቸኩየ ነው ወደስራ ፤ አስቴር እንጀራ አቅርቢላቸው እንጂ ይብሉ ቄሴ [ኮቴን እየለበሰ]

ቄስ ማሩ ፡ ፈልጌህ ነበር ገብረ ሚካኤል

ሰሎሞን ፡ ምን ነው በሰላም

ቄስ ማሩ ፡ እሱስ በሰላም ነው የምትሄድበት ጉዳይ ያን ያክል አስቸኳይ ነው ?

[ሰሎሞን ሊናገር ሲል አስቴር ከአፉ ነጥቃ]

ሰሎሞን ፡ እ

አስቴር ፡ ኧረ ያን ያክልም አያስቸኩል። ከጓደኞቹ ጋር ተቀጣጥረው ነው። ቢቀርም የሚያመልጠው ነገር የለም ።

[በዓይኑ ይገላምጣታል]

ቁስ ማሩ ፡ ያስ ከሆነ በል ቁጭ በል እናዉራ። ጨዋታስ ቢቀርም አይጎዳም በል ቁጭ በል።

ሰሎሞን ፡ እዉነት ነው እዉነት ነው አባቴ

ቁስ ማሩ ፡ አንቺም ቁጭ በይ ወለተ ጉበረኤል ሁለታችሁንም ነው የምፈልጋችሁ።[ትቀመጣለች] እንግዲህ ልጆቼ ምን መሰላችሁ ? ይሄ ማን ነው እዚህ ታች ሰፈር ባለፈው ሳምንት የሞተው ?

አስቴር ፡ አበበን ነው ?

ቁስ ማሩ ፡ አወ አበበ ። እንደው እንደዛ በድንገት መሞቱ አላሳዘናችሁም ?

አስቴር ፡ በጣም እንጅ ያን የመሰል ደግ ሰው በአጭሩ ተቀጨ

ሰሎሞን ፡ ደግ ሰው አይቆይ አባቴ እንደው እኔ ይገርመኛል ዝምብለን እንኳትናለን እንጅኮ የምንደክምለትን አናውቅምኮ

አስቴር ፡ ሰዉ ማለት እኮ ከንቱ ነው።

ሰሎሞን ፡ ከንቱ ለዚህ ከንቱ ስጋ እንደለፋን። ስንሞት አንዲት ቅንጣት ላይከተለን። ምናለ ብንመለስ

ቁስ ማሩ ፡ ጎሽ እግዚአብሄር ይመስገን። መልካም ተናገራችሁ ልጆቼ እንዲህ ከሆነማ እኔም የመጣሁበትን ጉዳይ አቀለላችሁልኝ። [ትንሽ ዝምይሉና]

እንግዲህ ሊጆቼ እስከዛሬ ከእናንተ ይመጣል ብዬ ብጠብቅም ፈራችሁኝ መሰል ዝም አላችሁ። በእርግጥ የኔ ስንፍናና ቸልተኝነት ዉጤት ነው። አምላኬ ይቅር በለኝ። የተሰጠኝ ስራ አልሰራሁበትም። እናንተን ወደ ንስሐና ወደ ቅዱስ ቁርባን ሳላቀርብ ሂደው አመታት ነጎዱ [ሰሎሞንና አስቴር ነገሩ ጉበቷቸው እርስ በርስ ተያዩ] ልጆቼ እንዳያችሁት ሰው ተሰባሪ ነው። ትላንት ከእኛ ጋር የነበሩት አሁን አፈር ተጭኗቸዋል። ተራው የእኛ ነው መጠራታችን አይቀርም። የተሰጠችን ፀሃይ እድሜ ሳትጠልቅ እና ሳይመሽ ሳይመሽ ልጆቼ በንስሐ እንፋጠን። አወ ልጆቼ የማሰብ የማስተዋል አእምሮን ተጠቅሞ አስቦ ፤ ኃጢአትን አምኖ ንስሐ ገብቶ ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆ ዕለተ ሞትን የመጠባበቅ ጊዜ ካለፉ አይመለስም ልጆቼ። ጊዜ ክፉ ነው ጊዜ ክፉ ነው አንዴ ካመለጠ ድጋሚ አይገኝም ልጆቼ። ከሞቱ በኋላ የመዳን እድል የለም ። እንደው ልጆቼ እባካችሁ ስለ ሕያው እግዚአብሔር ብየ ልለምናችሁ ንስሐ ገብታችሁ ቁረቡ ፤ እንደው ስለ ሕያው እግዚአብሔር ምክንያት ሳትደረድሩ እሺ በሉኝ ልጆቼ ገብረ ሚካኤል ወለተ ገብርኤል

ሰሎሞን ፡ አይ ማለቴ ልክ ነው እንዳሉት ጊዜው ክፉ ነው ካመለጠ ድጋሚ አይገኝም። ግንኮ አባቴ ዘሎ ወደ መቁረብ መግባት መቅሰፍት ነው የሚሆነዉ ። ንጽሕና ያስፈልጋል እኮ አይደለም እንዴት ?

ቄስ ማሩ ፡ “ ህመምተኞች እንጂ ጤነኞች መድሓኒት አያስፈልጋቸዉም ። ኃጣንን ወደ ንስሐ ልጠራ እንጅ ለፃድቃን አልመጣሁም ብሏል ባለቤቱ ። “ እንደዉም ቅዱስ ቁርባን ለኛ ለበደለኞቹ ነው የሚያስፈልገው ስርየተ ኃጢአት የሚገኘው በቁርባን በመሆኑ ። ከእኛ የሚጠበቀው ንስሐ መግባት እንጅ ማንም ቅዱስ ስጋዉን ክቡር ደሙን ለመቀበል የበቃ አይደለም ። ንስሐ ግባና ሌላዉን ለእግዚአብሔር ቸርነት ተወዉ ። ንፅህና ያስፈልገዋል ካልክማ መቼም አትቆርብም ።

ሰሎሞን ፡ እሱማ አወ ግን እንደዚህ በድንገት ንስሐ መግባቱ ጥሩ ላይሆን ይችላል ።

ቄስ ማሩ ፡ አሁን ተናዘዙ እያልኳችሁ አይደለም ። ተረጋግታችሁ አስቡበትና ጥሩኝ ቢበዛ 3 ቀን

ሰሎሞን ፡ 3 ቀንማ ምኑን ከምኑ አድርገነው ቄሴ 2 ወር 3 ወር ይስጡን እንጂ

ቄስ ማሩ ፡ 2 ወር ? የሰማዕቱ ያለሽ ። ለንስሐ ነገ ማለት ከኃጢአት ጋር ልቆይ ማለት ነው ። ሌላ ትርጉም የለዉም ።

አስቴር ፡ ልክ ነው አባቴ

ሰሎሞን ፡ ልክማ ልክ ነው ግን አሁን ይሁን ብል ራሱ በቀታይ ሳምንት ጀምሮ ለስራ ሌላ ቦታ የግዴታ ስለምሄድ አይመቸኝም። ባይሆን ከዛ በኋላ

ቄስ ማሩ ፡ እና ምን ያስቸግራል ይሄ አንተን ለመናዘዝ ያብቃህ እንጂ እዛው በሄድክበት ስግደቱንም ጸሎቱንም ትፈጽመዋለህ።

ሰሎሞን ፡ ስራው ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ስለሆነ ነው እንጂ ችግር አልነበረዉም ። ስመለስ ይሻላል

ቄስ ማሩ ፡ ኧረ ተዉ

ሰሎሞን ፡ አወ አባቴ ከዛ በኋላ ይሻላል ።

ቄስ ማሩ ፡ በል ካልክማ ምን አደርጋለሁ

ሰሎሞን ፡ አይጨነቁ አባቴ እኔ ራሴ መጥቼ ንስሐ እገባለሁ ።

ቄስ ማሩ ፡ አሄሄ በል እስኪ ይሁን

ሰሎሞን ፡ በቃ ከተስማማን እኔ ልሂድ እርስዎ ይጫወቱ

ቄስ ማሩ ፡ እንግዲያዉስ የአስራቱን ብር ፤ በባለፈውም አልከፈላችሁ የሁለቱ ወር መዶ ብር ነው ። ትኬቱን ልቁረጥላችሁ

[አንተ ክፉለው አንቺ ክፉይው በሚል እይታ ይተያያሉ]

አስቴር ፡ እኔስ ብር ጨርሻለሁ ሰሎሞን ይስጥዎት

[አውጥቶ ይሰጥና ተሰናብቶ ይወጣል]

ቁስ ማሩ እና አስቴር እያወሩ መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ሁለት

[መጋረጃ ሲከፈት ሰሎሞን እና አብርሃም መንገድ ላይ ሰክረው ይታያሉ]

አብርሃም ፡ የተባረከ ዓዉደ ዓመት

ሰሎሞን ፡ አንተ ሰዉየ ሰክረሃል መሰል ዛሬ እኮ ዓዉደ ዓመት አይደለም ቀኑ መስከረም 19 2007 ዓ/ም ነው

አብርሃም ፡ ላለው ሰው ሁልጊዜ ዓዉደ አመት ቢሆን ምን ችግር አለው ?

ሰሎሞን ፡ ኧረ ምን ችግር አለው ግን ታዉቃለህ አብርሽ በጣም ሰክረሃል እኔ እሻላለሁ

[ለማኝ ይመጣል]

ለማኝ ፡ ስለ ጻድቁ ስለ ቅዱስ ጎርጎርዮስ

አብርሃም ፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ይስጥልን ጊዮርጊስ የዛሬ አመት በሰላምና በጤና ያገናኘን

ለማኝ ፡ ስለ ሰማዕቱ ቅዱስ ጎርጎርዮስ

[አብርሃም ከት ብሎ ይስቃል]

አብርሃም ፡ አንተ በትክክል ቅዱስ ጊዮርጊስ ብለህ መጥራት ሳትችል ነው የምትለምንበት

ሰሎሞን ፡ ያዝ እንካ [ብር ይሰጠዋል]

ለማኝ ፡ ፃድቁ ይስጥልኝ [መሄድ ሲጀምሩ] ስንት ሰዓት ነው ልጆቹ ?

ሰሎሞን ፡ ሰዓት ሰዓት 11፡50 ከአናቷ ላይ አስር ጉዳይ ለ 12፡00

ለማኝ ፡ ረፍዶብሃል ሊጀ ቶሎ በል

ሰሎሞን ፡ የት ነው የረፈደብኝ [ከት ብለው እየሳቁ ይሄዳሉ] ት/ቤት ነው ?

ለማኝ ፡ አይ

ትዕይንት ሦስት

[መጋረጃ ሲከፈት አስቴርና ቴዲ ቁጭ ብለው እየጠበቁ]

ሰሎሞን ፡ ደህና አመሻችሁ ? ከዚህ ቤት

አስቴር ፡ ለምን አንደኛህን አድረህ አትመጣም ። ከሌሊቱ በ 7፡00 ትመጣለህ ?

ሰሎሞን ፡ ይሻላል ያውም እኮ ሶሲ እደርና ጥዋት ትሄዳለህ እያለችኝ ነዉ አስቴር ትበላኛለች ብየ የመጣሁት

አስቴር ፡ ቴዲ ሂድ ግባና ተኛ [ይሄድል]

ሰሎሞን ፡ እኔም ልግባና ልተኛ

አስቴር ፡ ኧረ ተው ሰሎሞን ተው ዛሬም ከዚያች ሴትዮ ትሄዳለህ [ታለቅሳለች]

ሰሎሞን ፡ አንቺ እኔ ጣጣ የለኝም ከፈለግሽ እዚህ ከቤት ነው የማመጣት ፤ እንፋታ ወይ ከደበረሽ

አስቴር ፡ እንፋታለን እስካሁንም ልጄን ይከፈዋል ብዬ ነው እንጂ ብትንትኑን አዉጥቼዉ ነበር።ነገ ወ/ሮ ጠሐይ ባለችበት ሁሉንም ነገር እበታትንልሃለሁ

ሰሎሞን ፡ ኧረረረ ጠሐይ ? ኧረ ጠሐይዋ እልም ይበል እሷ ሴትዮ ከቤቱ እንዳትመጣብኝ

አስቴር ፡ ቆይ ምን አጎደልኩብህ

ሰሎሞን ፡ ወይ ሙያ የለሽ ወይ መልክ የለሽ [መሳቅ ይጀምራል] እኔ እኮ ዝም ብዬ ሳይሽ ብግ መስለሽ ነው የምትታይኝ

አስቴር ፡ አይገርምህም ከዛች ከሶስናህ አስር እጅ እሻላለሁ

ሰሎሞን ፡ አሁን በጥፊ ሳላቀረናሽ ጥፊ ልተኛበት

ትዕይንት አራት

[መጋረጃ ሲከፈት ሰሎሞን በአጋንንት ተከቦ ይታያል]

[አስረው ይገርፉታል ። ይለምናቸዋል ። አይራሩለትም ።]

[ቅዱስ ጎርጎርዮስ ይመጣል]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እናንተ ርጉማን ከአገልጋዬ ምን አላችሁ ?

አጋንንት ፡ ጠላታችን ጎርጎርዮስ እዚህ ምን አለህ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ይህ የያዛችሁት ሰው የእናንተ አይደለም ።

ጋኔል 2 ፡ ምን ? ይህ ሰው የኛ ገንዘብ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም ። በገዛ ፈቃዱ የዘላለም ፍዳ የሚያመጣበትን ስራ በዘመኑ ሁሉ የሰራ ሰው ነው ። በህይወቱ ሙሉ የሰራው ስራ አይደለም ዛሬ በሞተበት ዕለት የሰራው ኃጢአት ታላቅ ነው ። ከሰው ሚስት ጋር ዘሙቷል ፤ ሚስቱን ተሳድቧል ፤ ካህን አቃልሏል ። በምንም ተአምር ሊድን አይችልም ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ይህ ሰው እኔ ለ 15 ዓመታት ከተቀበርኩበት በወጣሁበት እና ቃል ኪዳን በተቀበልኩበት ቀን ምፅዋትን ሰጥቷልና እናንተ ትወስዱት ዘንድ አላሰናብታችሁም ።

ጋኔል 3 ፡ ምፅዋት ሰጥቷል ? ይህ ሰው ለለመነው ሰው የሰጠው ሲለነዘነዘው እንጅ አስቦበት አይደለም ።

ጋኔል 1 ፡ በዛ ላይ ቀኑ የአንተ መታሰቢያ መሆኑንም በጭራሽ አላወቀም ። ይህ ፍትሐዊነት የጎደለው ፍርድ ነው አንስማማም ።

አጋንንት ፡ አንስማማም ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እኛ ሁላችንም በደለኞች ሳለን ነው በልጁ ሞት የታረቀን ። ማንኛውም ኃጢአት በእግዚአብሔር ቸርነት ፊት ሲቀርብ እሳት ላይ እንዳረፈ ገለባ ነው ። ለእኔ በገባልኝ ቃል ይህ ሰው ከእናንተ እጅ እንዲወጣ ፈቃዱ ሆኗል [ያማትብና ያባርራቸዋል] [ወደ ሰሎሞን] አንተ ሰው አሁን ስለ ኃጢአትህ ለእግዚአብሔር ምን ትመልሳለህ ። [መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት አምስት

[መጋረጃ ሲከፈት ሰሎሞን ከህልሙ ይነቃል]

ሰሎሞን ፡ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ (እየዳጋገመ) ህልም ነው ተመስገን ተመስገን ፈጣሬዬ ተመስገን (ይደጋግመዋል) [ይቅር በለኝ አምላኬ]

ትዕይንት ስድስት

[መጋረጃ ሲከፈት ቁስ ማሩ ሰሎሞንና አስቴር ይታያሉ]

ቁስ ማሩ ፡ [በረጅሙ ይተነፍሱና] እንግዳ ነገር ነው ። እዉነት ለመናገር በእርግጠኝነት ያየሀው ህልም ይሁን ራእይ ከእዚአብሔር ይሁን ከሰይጣን መናገር አልችልም ። ይህንን መለየት የሚችሉ ፍጹማን ናቸው።

በነገርከኝ ነገር ተነስቼ ግን ስገምት ከእግዚአብሄር ይመስለኛል ። ያየህው ሰው መስቀል የያዘ ከሆነ እውነትም ራሱ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርመያ ነው ። ምክኛቱም ከቅድስት አፎሚያ ታሪክ እንደተማርነው ሰይጣን በቅዱሳን እና በመላእክት አምሳል ሊገለጥ ይችላል ። መስቀል መያዝ ግን አይችልም ። በተለይ እዉነትም መስከረም 19 ለ 15 ዓመታት ከተቀበረበት የወጣበት የመታሰቢያ በዓሉ ነው ። በነገራችን ላይ ይህ ቅዱስ የማን ወንድም እንደሆነ ታዉቃላችሁ ?

አስቴር ፡ የማን ነው አባታችን ?

ቁስ ማሩ ፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርመያ የታላቋ ሰማዕት የቅድስት አርሴማ ትልቅ ወንድም ነው ።

አስቴር ፡ የሚገርም ነው አባታችን ቅድስት አርሴማ ታላቅ ወንድም እንደነበራት ሰምተን አናዉቅም ። በዛ ላይ ቅዱስ

ሰሎሞን ፡ ቁስ ማሩ አባቴ እኔ ያየሁት ህልም ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሳይጣን ብቻ ጊዜ ይፈታዋል የሆነው ሆኖ የዚህን ቅዱስ ታሪክ እንዲነግሩን እማፀነወታለሁ ።

ቁስ ማሩ ፡ የዚህን ታላቅ ቅዱስ ታሪክ ለመናገር ዕድሉን ስላገኘሁ መንፈሳዊ ኩራት ይሰማኛል ። ልጆቼ ህይወት ክርስቶስ ነው ። የህይወት ታሪክ መባል የሚገባውም ከክርስቶስ ጋር የኖሩት ነው ። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከእግዚአብሔር ጋር የኖረዉን የተቀደሰ ህይዎት ስነግራችሁ ከገድሉ ለነፍሳችሁ በቁኤት የሚሆን ትምህርት እንደምታገኙ በመተማመን ነው ። ቅዱሱ ከጻድቃን ከሊቃዉንትና ከቃቃሳት ዝርዝር ዉስጥ ይገኛል ። አባቶቻችን እንዲህ አይነት ሁሉንም አይነት የቅድስና ኑሮ የኖሩ አባቶችን ዓበይት ትጽፎ ይሏቸዋል ።

ከጻድቃን ዝርዝር ከሊቃዉንትም ከቃቃሳትም ወገን ከሁሉም ስለሚመደቡ ነው ። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርመንያ የተወለደው በ 3 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዘመነ ሰማዕታት ነው ። በቤተክርስቲያን ፍቅር ካደገ በኋላ ከደናግላን ጋር በገዳማዊ ህይወት ኖረ ።

ትዕይንት ሰባት

[መጋረጃ ሲከፈት ቅድስት አርሴማ እና ሌሎች ደናግል እየጸለዩ ይታያል ።]

ቅድስት አርሴማ ፡ አቤቱ ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን እኛን ባርያዎችህን ተሸግስትንና ጽናንትን አድለን ፤ መከራን ፈርቶ አንተን ከመካድ እርዳን አንተ ምሳሌ ሆነህ መከራን እንደተቀበልክ መከራ መስቀሉን ተሸክመን እንድንከተልህ ፈቃድህ ይሁን

[ከተንበረከኩበት ይነሳሉ]

መነኩሲት 1 ፡ እህታትችን እና መምህራችን አርሴማ ያንችን ምክር እንሻለን ። ለነፍሳችን የሚረባትን ምከሪን ።

መነኩሲት 2 ፡ አወ እህታችን አንቺ ከእኛ የበለጠ እምነት እና ጽናት አለሽ ።

[አንገቷን ደፍታ ትሰማለች ። ዉዳሴዋን አልወደደችዉም]

ቅድስት አርሴማ ፡ እህቶቼ እባካችሁ ሳይገባኝ እና ሳልሆን እያመሰገናችሁ ኃጢአቴን አታብዙት ። ብነግራችሁም አታምኑኝም እኔ በኃቲአትና በበደል የተመላሁ ሴት ነኝ ። ሁሉንም እግዚአብሔር ያዉቃል ። ወንድማችን ጎርጎርዮስ እየመጣ ነው ። አባታችንም አብረውት ስላሉ እነርሱ ይመክሩናል ።

[ቅዱስ ጎርጎርዮስ እና አበምኔቱ ይመጣሉ]

አበምኔት ፡ የእግዚአብሔር ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን እንደምን ዋላችሁ ልጆቼ

በአንድነት ፡ እግዚአብሔር ይመስገን

[በየተራ መስቀል ይሳለማሉ]

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ የተወደዳችሁ እህቶቼ እንደምታውቁት አባታችን ከፀሎትና ከስግደት ከቅዳሴ የሚተርፍ ብዙ ጊዜ የላቸዉም ። ለኛካላቸው አሳቢነት የተነሳ ነው ምክራቸዉን ሊለግሱን የመጡት መጠየቅ የምትፈልጉትን ነገር ጠይቁ ።

አበምኔት ፡ ተቀመጡ ልጆቼ [ይቀመጣሉ] በመጀመሪያ እንደምታውቁት ስለ እግዚአብሔር ስትሉ እንደሌሎች ሴቶች ክርስትናን ትቶ ሴትነትን በመጠቀም ከሰማዕትነት በመሸሽና የንጉስ ዕቁባት ሆኖ ከመኖር መከራን ችግርን ርሃብን መርጣችሁ የላመ የጣመ የሞቀ የደመቀ ከሌለበት ከዚህ ገዳም ስለገባችሁ የሰማዕታት አምላክ ጽናቱን ይስጣችሁ ከእናንተ የሚመጣዉን ጥያቄ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ

መነኩሲት 1 ፡ አባታችን የሚሰማንን ሁሉ በግልጽ እንድንወያይበት አስተምረዉናል ። እዉነቱን በቀጥታ ስናገር በጎሊናዬ የሚመላለስ ጥያቄ አለ ። እርሱም ለምን እኛ ክርስቲያኖች መከራን እንድንቀበል ጌታ ፈቃዱ ሆነ ማለት መከራ ሳይኖር እኮ ህጉን ትእዛዙን እየጠበቅን እየጾምን እየጸለይን መኖር እንችላለን ። መከራ ለምን ኖረ ?

መነኩሲት 2 ፡ የኔ ጥያቄ ለምንድን ነው በትክክል በወንጌል መኖር ያቃተን ? እዉነተኛ መንፈሳዊ ህይወት መኖር ለምን አቃተን ?

መነኩሲት 3 ፡ በገዳማዊ ህይወትም ሆነ በሰማዕትነት ዉስጥ ያለዉን መከራ እንዳንፈራ ምን እናድርግ ? ወይም ቆራጥነትን ጥብዓትን እንዴት ገንዘብ እናድርግ ?

ቅ/አርሴማ ፡ በክርስቲያኖች ላይ መከራና ግፍ የሚያደርሱትን ነገስታት መዉደድ እንዳለብን አስተምረዉናል ። ይህ እንዴት ይቻላል ?

አበምኔት ፡ አስፈላጊና ወሳኝ ጥያቄዎችን ነው የጠየቃችሁት ሁለቱን ጥያቄዎች እኔ ሁለቱን ደግሞ ልጇ ጎርጎርዮስ እንመልሳለን [ቅዱስ ጎርጎርዮስ ኧረ ይቅር በሚል ገፅ ያያቸዋል] ትእዛዝ ነዉ ልጇ እምቢ አትበል የመጀመሪያዉንና የአርሴማን ጥያቄ እኔ ቀረዉን አንተ እንመልሳለን ።

ወደ ጥያቄዋ ስንመለስ መከራ ለምን ኖረ ? ያለመከራ በዖም በጸሎት በስግደት በምጽዋት ትእዛዛቱን በመጠበቅ ለምን አንኖርም ። እንግዲህ ልብ ብላችሁ አድምጡኝ መከራ የእምነታችን መለኪያ ፈተና ነው ። ምን አልኳችሁ ?

ሁሉም ፡ መከራ የእምነታችን መለኪያ ፈተና ነው ።

አበምኔት ፡ ጎሽ እግዚአብሔር ይባርካችሁ ። ነገር በምሳሌ መዝሙር በሃሌ እንዲሉ አበው በምሳሌ እንየው። ለምሳሌ አንድ ተማሪ የፍልስፍናም ሆነ የውትድርና ትምህርት ቢማር ከተማረ በኋላ የተማረዉን ትምህርት ምያዝ አለመያዙን ለማወቅ እንዲሁም ያንን ትምህርት ከተማረ በጉዳዩ ብቃት ስላለው የተማረዉን በተግባር ገልጦ ለማሳየት ይፈተናል። የተማረ ሁሉ መፈተን አለበት። ከተማረ ጥያቄዉንም መመለስ አለበት ። ልጇ እኛም ወንጌልን ስለተማርን እንፈተናለን ። ክብር ይግባዉና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የሰራትን ወንጌል መፈተን አለበት ። በዝሙት ይፈተናል በመከራም ይፈተናል በሌላም መንገድ ይፈተናል ። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሁሉምነገር ገልጦ አስተምሮናል ። ማን እንደሆን ? ማን እንደፈጠረን ? ለምን እንደምንኖር ስለ ህይወት ትርጉም ? ስለ ሞት ትርጉም ስለ መዳረሻችን ሁሉን ነገር አመልክቶናል ። በምድር እስካለን ድረስ የምንመርጠው ህይወት ይህንን ጌታችን በምልአት ያስተማረዉን ትምህርት መሰረት ያደረገ ነው ። እንዴት መኖር እንዳለብን በስጋ ማርያም ተገልጦ በተግባር ኖሮ ቢያሳየንም ቅሉ ትምህርቱ ከእኛ ጋር መዋሃዱንና እየኖርንበት መሆኑን የምናዉቀው በፈተና ነው ። ለምሳሌ ዮሴፍን አስቡት የጴጥፋራ ሚስት አፈቀርኩህ ወደድኩህ ቢላ አብረን እንተኛ ባለችው ጊዜ ምን እንዳላት ታውቃላችሁ። " በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሰራለሁ " ልብ አድርጉ ልጆቼ ይህ የዮሴፍን እምነት እዉነተኝነት ለመለካት የመጣ ፈተና ነው። ዮሴፍ እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያይና በእግዚአብሔር ፊት የተሰወረ ነገር እንደማይኖር ተምሯል። ያውቃል። እግዚአብሔር ይያያል ብሎ ተምሯል። ምን ብሎ ልጆቼ ?

በአንድነት ፡ እግዚአብሔር ያያል

አበምኔቱ ፡ ምን ብሎ ?

[ይደግሙታል]

ጥሩ እንግዲህ ዮሴፍ እግዚአብሔር ያያል ተብሎ ተምሯል። ይህ ትምህርት ከዮሴፍ ጋር መዋሃዱን የእውነት የእውነት ዮሴፍ እግዚአብሔር ያያል ብሎ ማመኑን ለመለካት ዮሴፍ በዝሙት ተፈተነ። እዉነተኛ አማኝ ስለሆነ ትምህርቱ ከእርሱ ጋር ስለተዋሐደ ዮሴፍ እግዚአብሔር ያያል ብሎ ፈተናዉን አለፈ። በሌላ አነጋገር ተማሪ የተማረዉን መፈተን እንዳለበት ዮሴፍም እግዚአብሔር ያያል ብሎ የተማረዉን ልሌላ ሰው በሌለበት ከሴት ጋር ብቻዉን ሆኖ በዝሙት መፈተን ነበረበት። እኛም ወንጌልን ስለተማርን የተማርናትን ቃንጌል በተግባር እንድንኖራት ነዉና የተሰጠችን መፈተን አለብን። ጌታ በወንጌል ብዙ ነገር አስተምሮናል። ከመከራ ጋር አያይዞ ለማስረዳት ሁለት ነገር ብቻ ላንሳ። የመጀመሪያው ጌታ በወንጌል ሙሴ በኦሪት ያስተማረዉን አርቅቆና አብራርቶ ሲያስተምር "እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም ሃይልህ ዉደድ " ብሎ እርሱን እንዴት ባለ ፍቅር መውደድ እንዳለብን አስተምሮናል ታዲያ ስለ ፍቅረ እግዚአብሔር ስለተማርን እግዚአብሔርን ተውት ካዱት አለበለዚያ እናሰቃያቸኋለን እንገድላችኋለን ተብለን እንፈተናለን። እስከሞት እንድወደው ስለተማርን በሞት በመከራ እንፈተናለን። ሁለተኛው ደግሞ ጌታችን ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ ብሎ አስተምሮናል። ምን ብሎ ልጆቹ ?

በአንድነት ፡ ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ

አበምኔት ፡ አወ ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ህያው ይሆናል ብሏል። ታዲያ ትንሳኤና ህይወት ክርስቶስ መሆኑን ስለተማርን በእርሱ የእዉነት ያመነም ለጊዜው እስከ ትንሳኤ ዘጉባኤ በስጋ ቢሞትም በነፍስ ህያው ሆኖ ጸጋዉን ክብሩን ወርሶ እንደሚኖር ስላስረዳን ይህንን የተማርነዉን ትምህርት በመከራ በሞት እንፈተነዋለን ጌታ ትንሳኤና ህይወት እንደሆነ የሚያምን ሰው ሞትን መፍራት አይስማማዉም። ስለዚህ ስለህይዎት ክርስቶስ መማራችንና የእዉነት ማመናችን በሞት እንፈትነዋለን። ራሱ ህይወት በመሆኑ አስነሽ ሳይሻ ተነስቶ በኋላ እንዲህ በክብር ትነሳላችሁ ብሎ ከሞት በኋላ ትንሳኤ እንዳለ ስለተማርን ከሞትኩ በኋላ እነሳለሁ ብሎ ያመነ ክርስቲያን እንግዲያዉስ ና ሙት እና እየዉ ተብሎ ይፈተናል። ስለዚህ ወንጌልን ስለተማርን በመከራ እንፈተናለን። መከራ የእምነታችን የማመናችን መለኪያ ማረጋገጫ ፈተና ነው። ሁለተኛው መከራ ለምን ኖረ ? ለሚለው ምክንያት ከሰው ተፈጥሮ እና ከመንግስተ ሰማያት አንጻር ። ፈጣሪ አለማት እግዚአብሔር ሲፈጥር ከአገልግሎት አንጻር በሦስት መደብ ፈጥሯል። የመጀመሪያው መደብ ፍጥረታት ለሌላው መደብ ፍጥረት ጥቅም የሚሆኑ ነገር ግን ራሳቸው ጥቅምም ሆነ ጉዳት የማያገኛቸው ናቸው።ለምሳሌ ዉሃን ሌላው ይጠጣዋል። ለራሱ ግን ዉሃነቱ አይጠቅመዉም አይጎዳውም። ዉሃ አእምሮ ህይወት የለዉምና። በሁለተኛው መደብ ያሉ ፍጥረታት ደማዊት ነፍስ ያላቸው ለሰው አገልግሎት የሚሰጡ ነገር ግን ተስፋ ትንሳኤ የሌላቸው ቢያጠፉም ርደኛተ ገሃነም የሌለባቸው ናቸው። ለምሳሌ አህያን ሰው ሁሉ ይጭነዋል። በሬን ሰው ሁሉ ያርሰዋል። አህይና በሬ ሰውን ቢያገለግሉም ቢደክሙም ደክመው ይቀራሉ እንጂ ዋጋ አያገኙም። መንግስተ ሰማያት አይወርሱብትምና። ከሰው መሬት ከሰው እህል ቢገቡም ለጊዜው ቢደበደቡ እንጂ የሰው እህል አወደማችሁ ተብለው ገሃነም

አይፈረድባቸዉም። ደማዊት ነፍስ ቢኖራቸውም አእምሮ የላችውምና። ሦስተኛው መደብ ደግሞ ሰዉና መላእክት ናቸው። የሚያስብ የሚያዉቅ አእምሮ ስላላቸው አዉቀው አስበው ለህጉ ለትዕዛዙ ቢገዙ ተስፋ ትንሳኤ አላቸው። እያወቁ ቸላ ብለው በገዛ ፈቃዳቸው ህጉን ትዕዛዙን ቢያፈርሱ ፍጻሜ በሌለው ዘመን የገሃነም መከራ አለባቸው። ስለዚህ ሰው ቢሰራ ሊሸለም ቢያጠፋ ሊቀጣ አዋቂ ሆኖ ተፈጥሯልና መንግስት ሰማያትን በመከራ ተፈትኖ ምግባር ትሩፋት ሰርቶ ቢኖር ሽልማት ሆና ትሰጠዋለች። ልቡን ቢያደነድን መሪር ገሃነመ እሳት ትጠብቀዋለች። ስለዚህ መከራን የምንቀበለው ዋጋችንን እንኳን ገብተዉባት ሲለሱ ሲያዉሩ ደስታን የምጸጠውን ሰማያዊት ሀገር ለመዉረስ ነው። እራሱ ባለቤቱ እንዳለው " እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን። የህይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።" የህይወት አክሊል የተባለ በቁሙ ከራስ በላይ የሚቀመጠዉን አይደለም። ይህማ ምድራዊ ክብር ነው። ይህይወት አክሊል የተባለች መንግስተ ሰማያት ናት። በንጽጽር ሲያስቀምጠው ነው። የሮጠ የቀደመ አክሊል እንደሚሰጠው ተጋድሎ ላሸነፈ ሽልማት ሆና ስለምትሰጥ አክሊል ትባላለች። እናም ሊጆቼ መከራዉን የምንቀበለው ለምን ነው ? ባለቤቱ ምን ስላለን ነው። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን መንግስተ ሰማያትን እሰጥሃለሁ።"

[ይቀመጣሉ][ቅዱስ ጎርጎርዮስ ይነሳል]

ቅ/ጎርጎርዮስ ፡ አባታችን የተናገሩትን ሰምታችኋል። ብዙ ነገሮችን የያዘ ነው። ጥቂት ነገር ለመጨመር ያክል ነው የተነሳሁት። እዉነተኛ መንፈሳዊ ሰው መሆን ለምን አቃተን ስለሚለው አንድ ነገር ብቻ ልናገር። የመንግስተ ሰማያት ዉበት ስላልማረከን ነው እህቶቼ መንፈሳዊ ሰው መሆን ያቃተን። መንግስተ ሰማየት የምትሰጥበት ቀን ስላልደረሰ ስላላየናት ታስቦ የማይደረስበትን ጣዕሚን በቃለ መጽሐፍት ሰምተን እንድንማረክላት ዓለማዊ ነገሮችና ዓለማዊ ምኞቶች ልባችንን ስላጨቁን የልባችን ጉልበት ደካማ ሆኗል። እህቶቼ የድንግልና የንጽህና ነገር እያለ የዝሙት ነገር የበለጠብን የትግሃ ሌሊት ጣዕም እያለ የእንቅልፍ ጣዕም በለጠብን ? የመጾም የመስገድ ነገር እያለ የመብላት የዉበት ነገር ጡንቻን የማዳበር ነገር በልለጠብን መዝሙር እያለ ዓለማዊ ዘፈን በለጠብን ንስሐ መግባት ራስን ማንጻት እያለ በቅዱስ ቁርባን ተወስኖ የመኖር ነገር እያለ ልማዳዊ ህይወት መብላት መጠጣት ድግግሞሻዊው የዕለት ከዕለት ነገር በለጠብን ለምን ይመስላችኋል ዓለማዊ የሆኑት ነገሮች በሙሉ ቀድመዉ ልባችንን ስለያዙት ለመንፈሳዊ ተግባራት ፍላጎት አይኖረውም። ዝሙትን ቀድመን ከለመድን የድንግልና የቅድስና ነገር አይታየንም። ሌሎችን ነገሮችም እንዲሁ። ስለዚህ እግዚአብሔርን የእዉነት መዉደድ ስንጀምር ኃጢአትን የእዉነት መጥላት እንጀምራለን። ልባችን የመንግስተ ሰማያትን ክብር ማየት ሲችል ዓለማዊውና ብላሽ ኃላፊ ጠፊ የሆነዉን ነገር መናቅ እንችላለን።

ቅ/አርሴማ ፡ ታላቁ ወንድማችን ዋናው ጥያቄ ዓለማዊነት ያደከመዉ ልባችን እንዴት አድርጎ የመንግስተ ሰማያት ነገር ይገባዋል ነው። ችግሩን እንዳብራራህልን መፍትሔዉንም ንገረን።

ቅ/ጎርጎርዮስ ፡ በየቀኑ የቅዱሳኑን ዜና ህይወት እናንብብ። ያኔ ቅዱሳኑን ማድነቅ እንጀምራለን ቅዱሳኑን ስናደንቅ እነሱን ለመምሰል እንወዳለን። ተጋድሏቸው ስለሚማርከን እነሱን ለመምሰል ወደድን ማለት ቅድስናን ንጽህናን በአጠቃላይ መንፈሳዊ ህይወት ወደድን ማለት ነው። ያን ጊዜ ልባችን ከዓለማዊነት ይላቀቅና መንፈሳዊነትን ይጀምራል። በዚህ ልባችንን ወደ ልዕልና መንግስተ ሰማያት ማስማረክ እንችላለን።

በእዉነተኛ ከልብ በሆነ ልመናም ልባችንን ከዓለማዊ የምኞት ባርነት አላቆ ፈዉሶ የተረጋጋ የሰከነ መንፈሳዊነትን እንዲሰጠን ከለመነው ይሰጠናል።

መነኩሲት 2 ፡ እዉነተኛ ከልብ የሆነ ጸሎትን ለመጸለይስ ምን እናድርግ ?

ቅ/ኅርኅርዮስ ፡ እዉነተኛ ጸሎት ማለት ዓለማዊ ነገሮችን ዘንግቶ የሚጸልዩት ነው። ለጸሎት ከመቆማችን በፊት መረጋጋት እና አእምሯችንን ማሳረፍ አለብን። ስንሰራው በነበረ ስራ አሳብ አእምሯችን ስለሚያዝ ሃሳባችን ሰብስበን መጸለይ ያቅተናል። ስለዚህ ተረጋግተንና አእምሯችንን ከሚወጡ ከሚወርዱ ሃሳቦች አሳርፈን ዝም አናሰኘው። ዉስጣችን ጸጥ ካለ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት መቆማችንን እናስብ።እየሰማን እንደሆነ ፊታችን ከአጠገባችን እንዳለ በፊቱ እንደቆምን ሲሰማንና ሲታወቀን ከበድ ሲለን ያን ጊዜ እዉነተኛ ጸሎት ይባላል። የምንለምንዉን ነገር ደግሞ ከልብ የምንሻው መሆን አለበት። መንፈሳዊነትን ከልብ ሳንሻ ስጠን ብንለው አይሆንም። ስለዚህ ልባችንን ክትት አድርገን ከዓለማዊነት ከኃጢአት እንዲያላቅቀን እንለምነው። እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ባፈሰሰችው እንባ ከኃጢአት እድፍ እንድታነጻን። ስደቷ አጋንንትን ከልባችን ከህይወታችን እንዲያሳድድልን ርሃቧ ለነፍሳችን ጥጋብ እንዲሆነን ችግሯ የመንፈሳዊነትን ጎደሎ እንድትሞላልን እንማጸናት። የቀሩትን ጥያቄዎች አባታችን ይመልሱልናል።

[አበምኔቱ እየተነሱ }

አበምኔት ፡ ለዛሬ በዚህ ይበቃናል ትምህርት ሲበዛ ስልቹነት እና ዝንጉነት በልቡና ያድራል። የሰማነዉን በልቦናችን ያሳድርልን። ሰሞኑ ከመቅረት ይሰዉረን በሉ እኔም ወደ በዓቴ ልግባ የምትፈልጉት ነገር ካለ ለወንድማችሁ አሳዉቁት።

[ይወጣሉ]

ቅ/ኅርኅርዮስ ፡ የምትፈልጉት ነገር አለ ? እህቶቼ

ቅድስት አርሴማ ፡ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን የጎደለን ነገር የለም

መነኩሲት 1 ፡ በእናንተ ምክርና ጸሎት በመልካም ሁኔታ ላይ ነው ያለነው።

መነኩሲት 3 ፡ አርሴማ ለአንተ የሥጋ እህትህ ብትሆንም ሁላችንን እኩል በማየት ስለምታጽናናን ዋጋህን ይክፈልህ።

መነኩሲት 2 ፡ አወ ታላቁ ወንድማችን ስለቅንነትህ እግዚአብሔር ዋጋህን ይክፈልህ

ቅዱስ ኅርኅርዮስ ፡ እግዚአብሔር እንዲከፍለኝ ከፈለጋችሁ እናንተ አሁን መክፈላችሁን አቁሙ

[ይሄዳል]

መነኩሲት 2 ፡ ወንድማችን አስቀየምነው

መነኩሲት 1 ፡ ኅርኅርዮስ በጭራሽ አይቀየምም ከንቱ ዉዳሴዉን ስለሚጠላ ነው።

ቅድስት አርሴማ ፡ አሁን ሁላችንም ወደየ በዓታችን እንሂድ ከዛ በፊት ግን ሰዓት ገና ስለሆነ መጸለይ አለብን።

[እየጸለዩ መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ስምንት

[መጋረጃ ሲከፈት ንጉስ ዲዮቅልጢያኖስ ከአማካሪዉና ከወታደሮቹ ጋር ይታያል]

ዲዮቅልጢያኖስ ፡ ሴት ሴት ሴት ቆንጆ ሴት አምጡ እባካችሁ ለጋ ለግላጋ የምታስጎመጅ ቆንጆ በሴት ፍላጎት ዉስጤ ተቃጠለኮ ነዉ የምላችሁ ደንቆሮ ጠቅላላ ሮምን አስሳችሁ ቢያንስ አንዲት ሴት ማምጣት አቃታችሁ። ተናገሩ ምን እንደ እባብ አንገታችሁን ትቀብራላችሁ እናንተ ቅራቅንቦዎች

ወታደር 1 ፡ ንጉስ ሆይ የአቅማችን ሞክረን ነበር

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ የራሳችሁ ጉዳይ ካዝጣችሁም የራሳችሁ ጉዳይ ነው። ብቻ አምጡልኝ (በጩሀት)

ካህነ ጣኦት ፡ ንጉስ ሆይ ይረጋጉ ረጋ ይበሉ ለምን ይጨነቃሉ እኔ ታላቁ የአምልክቶቻችን የአፖሎና የአርጤምስ ካህን እያለሁ ለምን ይጨነቃሉ አማልክቱን ጠይቄ ቆንጆ ሴት የት እንዳለ ማወቅ እንደምንችል ረሳችሁ ?

[ዲዮቅልጥያኖስ ፈገግ ይላል]

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ይህንን መች አስታወስኩና እዉነትም አንተ ታላቅ ካህን ነህ አማልካኞች ይሰሙሃል።

ታዲያ ጠይቅልኝ

[ካህን ጣኦት ወደ ጣኦቲቱ ይዞራል]

ካህነ ጣኦት ፡ የአማልክቶቻችን የአፖሎና የአርጤምስ መንፈሶች ሀርደሽ ማርኩሽ ንገሩኝ ቆንጆ ሴት የት ነው ያለው ንገሩኝ ሃርዲሽ ማርኩሽ ሃርዴሽ ማርኩሽ ዉሕ ሃርዴሽ ማርኩሽ ዉሕ ምን ? ምን አላችሁ ? ህ _____ ንገሩኝ ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ ቆንጆ ሴት ያለበትን አወቅሁት

ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ኧረ ባክህ እዉነትክን ነው እኮ ንገረኝ ልወቀዉና ላስመጣት አስመጥቼ (ወይኑን እያነሳ) የቆንጆ ሴት ጥማቴን እንደዚህ ወይን (ይጠጣል) ቅዝቅዝ ታድርግልኝ። ታግባኝና ትገላግለኝ ቶሎ በል የተከበርከው ቶሎ በል

ካህነ ጣኦት ፡ እንግዲያዉስ የተከበርከው ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ አንተ አግብተህ እቁባት እንዳታደርጋቸው ፊርተው የተደበቁ ቆነጃጅት ክርስቲያኖች አሉልህ። ወደ መኖሪያቸው ሰዓሊያንን ልከህ ሁሉን ይሳሏቸዉና የፊለግካቸዉን መርጠህ ላስመጣ የወደድከዉን ካደረክ በኋላ በእሳት አቃጥለህ አጥፋቸው ራስህንም አማልክቶችንም አስደሰትካቸው ማለት ነው።

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ለዚህ ቅዱስ ሰው 200 የወርቅ ምዝምዝ ስጡልኝ እባካችሁ እናንተ ሂዱና ስላችሁ አምጡልኝ አሁኑኑ

ወታደር 2 ፡ ታዛዥ ነን ንጉስ ሆይ [ይወጣሉ]

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ትንቢትህ እዉነት ከሆነና ቆንጆ ሴት ከተገኘ የማደርግልህን አዉቃለሁ። አሁን በአማልክቱ ፊት ተደፍተህ ቅንጅ ሴት የማግኘት ዓላማቸዉን እንዲያሳኩላቸው ለመለክተኞቼ ለምንላቸው

ካህነ ጣኦት ፡ የተከበራችሁ አማልክት ቆንጆ ሴት ለንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ የአማልክቱ መንፈሶች ሃርዲሽ ማርኩሽ ቆንጆ ሲኤት ቆንጆ ሴት ቆንጆ ሴት

[መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ዘጠኝ

[መጋረጃ ሲከፈት ቅዱስ ጎርጎርዮስ እየጸለየ ይታያል]

ቅ/ጎርጎርዮስ ፡ አቤቱ ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛና በደለኛ ሆኜ ሳለ ጻድቅ አድርገው ከሚያስቡኝሰዎች አድነኝ ጌታ ሆይ በመስቀል ላይ በተቀበልከው መከራ ከመከራ ኃጢአት አድነኝ እርኩስ ምራቅ የተተፋበት ፊትህ በኃጢአት የጠቆረ ገጼን ያጥራው ወደ ፈያታዊ ዘየማን ዘንበል ያለ ራስህ አጋንንት በበትረ ኃጢአት ደብድበው የጣሉትን ራሴን ያንሳው።

[አርሴማ ቅድስት ገብታ ትመለከተዋለች] በመስቀል ላይ የተዘረጋ ሥጋህ አጋንንት በክፉ ምክራቸዉ እየሳቡ ወደ ገሃነም የሚያወርዱትን ልቦናየን ወዳንተ ይመልሰዉ አወ ጌታ ሆይ ልቤ ወደ ገሃነም የሚያወርደዉን ኃጣአት ወዶ እየሄደ ነውና በመስቀል ላይ የተዘረጋ ቅዱስ ሥጋህ ልቤን ወደ አንተ ይመልሰው። ልቤን ወደ አንተ ይመልሰው ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታዉቃለህ ልምን አታለቅስም ትለኝ እንደሆነ ተቆርቁሬ ወዳንተ መመለስ የሚችል የሚያለቅስ ልቦና የለኝም ጌታ ሆይ ልቦናየ ይህን ዓለም በማሰብ ደከመ አቤቱ የሃብታት ሁሉ መገኛ አንተ በቸርነትህ ራርተህ የሚመለስ ልቦና ስጠኝ እባክህ አምላኬ በቸርነትህ ራርተህ ተነሳሂ አድርገኝ አሜን

[እህቱ መኖሯን ያያል] መጥተሻል እንዴት አርሴማ ?

ቅ አርሴማ ፡ የአሁኑን ጸሎት ከወዴት አገኘህው ?

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ በመጽሃፈ መነኮሳት ዉስጥ ያለ ነው። እኔም ወድጀዋለሁ ።

[ሌሎች ደናግል ይቀርባሉ]

ቅ አርሴማ ፡ ለምን እንዲህ አልሽ ? አባቶቻችን የምንጽልየው ጸሎት ከመጻህፍት እንዲሆን አዘዉናል። ምክኛቱ ደግሞ እኛ ደካሞች የምንለምነዉን ስለማናዉቅ ተገቢ የሆነ ጸሎት ያቀረቡ የቅዱሳን አባቶቻችን እናቶቻችን ጸሎት እየጸለይን እንድንጠቀም ነው ። እኔ ግን ከደካማነቴ ብዛት የተነሳ አንዳንድ ጊዜ

በመጽሓፍት ስጸልይ የኔን ሃሳብ አልገልጽኝ እያለና የሊላ ሰው ጸሎት እየጸለይኩ መስሎ ይሰማኛል ። የአሁኑ ጸሎት ኝ የነን ችግር የሚገልጽ በመሆኑ ብጸልየው ደስ ይለኛል ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ የሊሎች መጻሕፍትም ቢሆን የኛ ጸሎት መስሎ የማይሰማን ትርጉሙን ስለማናዉቀው ነው።

መነኩሲት 1 ፡ በመጻሕፍት ስንጸልይ ጸሎቱ የኛ መስሎ እንዲሰማንና ማንበብ ሳይሆንብን መጸለይ የምንችለው እንዴት ነው ?

[ወደ አበምኔቱ ይዞራል። እርስዎ ይመልሱት በሚል]

አበምኔት ፡ ይህ የሚሻለው በሁለት ነገር ነው። የጸሎቱን ትርጉም በመርሳት እና የራስን ችግር በማሰብ ነው። ለምሳሌ ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት " አጥንቶቼ ታዉከዋልና ፈዉሰኝ " ብሏል። አንድ ሰው ዳዊት ሲደግም ይህን ቃል ያገኘዋል። ይህ ሰው ማድረግ ያለበት መጀመሪያ ትርጉሙን መረዳት ነው። የዚህ ቃል ትርጉም ምን መሰላችሁ እንደምታዉቁት የኛ የጀርባ አጥንታችን ከታወከ ከተንሸራተተና ከተዛባ መቆም መራመድ ተስተካክሎ መቀመጥእንኳን ያቅተናል። የዚህ መንፈሳዊ ትርጉም መንፈሳዊነቴ ተናግቷል። መሰረቴ ፣ እምነቴ ፣ እግዚአብሔርን መፍራቴ ፣ መጸጸቴ ፣ የጸሎት ህይወቴ ተናግቷል ነው። ሰው እነዚህን ነገሮች ካጣ መነፈሳዊ ሆኖ መኖር አይችልም። እምነት እግዚአብሔርን መፍራት ጸጸትና የጸሎት የመንፈሳዊ ህይወት የጀርባ አጥንቶች ናቸው። እነዚህ ከተናጉ መንፈሳዊነት ይቀራል። የሚጸልየው ሰው ይህንን ከተረዳ በኋላ የራሱን ችግር ማሰብ ቀጣዩ ነገር ነው። ማለትም ልቡ እንደደነደነ እምነቱ እንደጎደለ እግዚአብሔርን መደፋፈርና በድፍረት ኃጢአት መስራት መልመዱን ከጸሎት መራቁን በኃጢአት መደስት መጀመሩን ያስብ ያን ጊዜ ጸሎቱ የሱ ወደመሆን ይመጣል። አጥንቶቼ ታዉከዋልና ፈዉሰኝ ሲልም መንፈሳዊ የጀርባ አጥንቱ እንደተናጋ እየታወቀዉና እየተሰማው ፈዉሰኝ እያለ አጥብቆ ወደ እግዚአብሔር ይጮሃል።[ከቅዱስ ጎርጎርዮስ ጋር በሹክሹክታ ያወራሉ] በሉ እንግዲህ ልጆቼ እኔና ጎርጎርዮስ ከእናንተ መካከል መሪ ልንመርጥ አስበናል። እኔ በበኩሌ አርሴማ የደናግላን መሪ እንድትሆን ወስኛለሁ።

ቅድስት አርሴማ ፡ ምን ? ኧረ አባቴ በጭራሽ አልሆንም።

አበምኔት ፡ በናንተ በኩል ተቃዉሞ አለ ?

መነኩሲት 2 ፡ በጭራሽ አባታችን አርሴማ ለእኛ አራአያ መሆን የምትችል በእግዚአብሔር ጸጋና ሞገስ የተሞላች እህታችን ናት።

ቅድስት አርሴማ ፡ እኔ አልችልም እህቶቼ እባካችሁ ልኑርበት እንኳን እናንተን ልመራ ራሴን መግዛት ያቃተኝ ሰው ነኝ

አበምኔት ፡ መታዘዝ ከመስዋዕት ይበልጣል

ቅድስት አርሴማ ፡ የሚሆንልኝ ቢሆን ኖሮ ምንም ችግር አልነበረዉም። እባካችሁ እመኑኝ እኔ አቅሙ የለኝም።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን

መነኩሲት 3 ፡ አወ እህታችን ፈቃደ እግዚአብሔርን ተቀበይ

[አርሴማ በሃዘን]

ቅድስት አርሴማ ፡ አሜን እግዚአብሔር ያለው ይሁን

አበምኔት፡ በጸሎት እንጠይቅ

ትዕይንት አስር

[መጋረጃ ሲከፈት ንጉስ ድርጣድስ ሰው እያስገረፈ ይታያል]

ድርጣድስ ፡ በለው ትንሽ ዝቅ እሱ ላይ እሱ ላይ አዎ ድግመው

ተገራፊ ፡ ኧረ ባካችሁ ተዉኝ ኧረ እናቴ _____

ድርጣድስ ፡ እናትክን ማሰብ የነበረብህ አስቀድመህ ነበር። ልብሱን ግለጥና መግረፍክን ቀጥል

ወታደር 1 ፡ ታዛዥ ነኝ ንጉሴ

ድርጣድስ ፡ እንደሱ ደህና አድርገህ ልጠህ ልጠህ ጣልልኝ

[እየበላና እየጣጣ ይቆያል። ከቆይታ በኃላ] ይበቃዋል ወደ ዚህ አቅርቡት

[ያቀርቡታል]

አንተ የማትረባ እንዴት ብትደፍር ነው ከታላቁ ንጉስ ከእኔ ከድርጥድስ ከአርመንያው ጌታ ቤተ መንግስት የምትሰርቀው ?

ተገራፊ ፡ ንጉስ ሆይ ይቅርታ ያድርጉልኝ ርቦኝ ነው የሰረቅኩት

ድርጣድስ ፡ ምን ? ከቤተ መንግስት ዉስጥ ባርነት ተቀጥረህ የምበላው አጥቼ ስትል ትንሽ አታፍርም ? ክብር ለአማልክቱ ይሁንና ቤቴ እንኳን እንዳተ ላለው መንቋዳ ባሪያ ቀርቶ አለምን የሚመግብ በረከት አለው።

ተገራፊ ፡ ንጉስ ሆይ ልክ ነወት ነገር ግን ወታደሮቹ ምግቤን እየቀሙኝ ነው።

ድርጣድዮስ ፡ አንተ ታዲያ ወንድ አይደለህም ሲቀሙህ ዝም ብለህ ታያለህ ? ይህንን ሰው ተጨማሪ 40 ጅራፍ ግረፉና ከቤተ መንግስት አባሩት

ወታደር 2 ፡ ንጉስ ሆይ ይህ ሰው የብዙ ሙያወች ባለቤት ነው። የአትክልት ቦታውንና ለእርስዎ የሚቀርበዉን ምግብ በጥሩ ሁኔታ ሲያዘጋጅ የነበረ እርሱ ነው። እርሱን ካባረሩት የምግብወ ነገር አደጋ ላይ ይወድቃል

ድርት፣አድዮስ ፡ [ያቅማማና] ከአማልክቱ ቀጥሎ የማገለግለው ሆዴን ነው። ቢሆንም እኔ ድርጣድስ አንድ ተራ ባሪያ አልለማመጥም አስወጡት [በጥፊ ብለው ያባርሩታል]

ትሰሙኛላችሁ ሆዴን እንዲከፋው አልፈልግም። ጥሩ ምግብ ማዘጋጀት የሚችል ብሪያ ሴትም ሆነ ወንድ አምጡልኝ ! ብቻ እየጣፈጠኝ ልብላ።

[ተመልሶ ይቀመጥና መብላቱን ይቀጥላል። መጋረጃ ይዘጋል።]

ትዕይንት አስራ አንድ

[መጋረጃ ሲከፈት እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ እየጸለዩ ይታያል]

[ወታደሮቹ ዘዉ ብለው ይገባሉ]

ወታደር 1 ፡ ማንም ሰው እንቅስቃሴ ለማድረግ እንዳይሞክር። ሁላችሁም ባላችሁበት

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እናንተ እነማን ናችሁ ? ከእኛ ምን ትፈልጋላችሁ ?

ወታደር 2 ፡ ከእናንተ ምን እንፈልጋለን። እኛ የምንፈልግ ሴቶችን ነው። እንደዉሃ ሳልደፋችሁ እናንተ ሁላችሁ ከፊታችን ዘወር በሉ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አይሆንም እኔን ግደሉኝ እነርሱን ተዋቸው

አበምኔት ፡ አይሆንም እኔን አስቀድመኝ !

ወታደር 2 ፡ ሰዎቹ ምን ነክቷቸዋል። ትሰማላችሁ ለመግደል ብንመጣ ኖሮ እስካሁን ድምጥማጣችሁ እልም ብሎ ነበር።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ታዲያ ለምን መጣችሁ ወንድሞቼ ?

ወታደር 1 ፡ ወንድሞቼ ? [ከት ብለው ይስቃሉ] እዚህ በረሃ ዉስጥ እየኖራችሁ እብዶች ባትሆኑ ነበር የሚገርመን ! እኛ የመጣነው ትልቅ የምስራች ይዘን ነው።

አበምኔት ፡ ምንድን ነው እሱ ልጆቼ ?

ወታደር 2 ፡ ወልደህናል ሰዉዬ ! ላማንኛው የምስራችሁ ከመናገራችን በፊት ሴቶችን ማየት ይኖርብናል። ፈቀቅ በሉ እኛቸው !

[በጥርጣሬ ፈቀቅ ይላሉ]

ወታደር 1 ፡ ኧረ መልክ ኧረ ዉበት [ከአርሴማ ሲደርስ] በለው በለው ኧረረ ! [በደንብ እየተዘዋወረ ያያታል] በጣም ጥሩ አሁን በደንብ ስላየሁሽ ለመሳል መልክሽ አይጠፋኝም። ለመሆኑ ስምሽ ማን ነው ?

መነኩሲት 1 ፡ አርሴማ ትባላለች። ለምን ፈለግህው ?

ወታደር 1 ፡ አንቺን ያናገረች የለም። ዶሮ

ወታደር 2 ፡ ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ ቆንጆ ሴት አግብቶ አንደላቋት ሊኖር ይፈልጋል። አንቺ ለዚህ የማይገኝ እድል ብቁ ትመስያለሽ።

አበምኔት ፡ አርሴማ የመንግስት ሰማያት ሙሽራ እንጂ የንጉስ ዕቁባት አትሆንም።

ወታደር 2 ፡ ሰዉየ ነገር ትፈልጋለህ ? [ሰይፉን ይመዛል]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ [በመካከል እየገባ] አያስፈልግም ወንድሜ አያስፈልግም ! ተመካክረን ዉጠቱን እናሳዉቃችኋለን ! ጊዜ ብቻ ስጡን ! ጠብ አያስፈልግም።

ወታደር 2 ፡ [አርሴማን ተጠግቶ] የዚህን ሽማግሌ ምክር አትስሚው ! እሱ እድሜዉን ጨርሷል ! የሚታየው የሚሞትበት ቀን ብቻ ነው። የሚጠብቀው ደስታ የለም አንቺ ግን ገና ወጣት ነሽ በዛ ላይ ቆንጆ ሴት ! ከእሁኑ ዲዮቅልጥያኖስን አግብተሽ የምትኖሪያቸዉን በቅንጦትና ምቾት የተሞሉ ቀናት አስቢ። የዚህን ራስ ወዳድ ሽማግሌ ምክር ሰምተሽ ብትሞኝ ደግሞ የሚጠብቅሽን ስቃይ አስቢው። ዓይንሽ ይወጣል። ቆዳሽ ይላጣል። ጡትሽ በህይወት እያለሽ ይቆረጣል። ስቃዩን አስቢው ከባድ ነው አትችይዉም። ያገኘሽዉን እድል ተጠቀሚበት። ምርጫው ያለው በእጅሽ ነው። ከሳምንት በኋላ እንመጣለን !

[ይወጣሉ]

ቅድስት አርሴማ ፡ አሁን ምን ይዉጠኛል ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እኛ ሁላችንም ከጎንሽ ነን። የሚመጣዉን ሁሉ አብረን እንቀበለዋለን።

ቅድስት አርሴማ ፡ እንደዛ መሆን የለበትም። በኔ ችግር ማንም ሰው እዲጎዳ አልፈልግም።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ችግርሽ ችግራችን ነው። አይዞሽ እህታችን ሁሉንም በኔ ጣይው ! መፍትሔዉን እኔ አስብበታለሁ። አሁን ወደ ሥራችሁ ሂዱ መፍትሔ ሳገኝ እነግራችኋለሁ።

መነኩሲት 1 ፡ አዎ እህታችን ! ብቻሽን አንተዉሽም ! ጎርጎርዮስ መፍትሔ እስኪያገኝ ወደ በዓትሽ ግቢና እረፊ

መነኩሲት 3 ፡ እሺ በይ አርሴማ

[ይወጣሉ]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አባታችን እርስዎም ይሂዱ ! መፍትሔዉን እኔ ራሴ ልጨነቅበት !

አበምኔት ፡ ብቻህን ባልተዉህ ደስ ይለኛል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ግዴለም ይሂዱ ባይሆን መፍትሔዉን እንዲገልጽልኝ በጸሎት ይርዱኝ !

አበምኔት ፡ መልካም ! እግዚአብሔር ይርዳህ ! [ይሄዳሉ]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ጌታ ሆይ የእህቶቼን ነገር አደራ ! ከዚህ ፈተና ማምለጫዉን መንገዱን አመልክተኝ ! [እየተንጎራደደ ያንሰላስላል] [ከቆይታ በኋላ] አወ ወደ አርመንያ እንሰደዳለን ! ሮምን ለቀን ወደ አርመንያ እንሰደዳለን ! መፍትሄ አገኘሁ እህቶቼ [ይወጣል] [መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት አስራ ሁለት

[መጋረጃ ሲከፈት ዲዮቅልጥያኖስ ስዕሉን ይዞ ይታያል]

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ እዉነትም አማልክቱ ነግረዉሃል አንተ ቅዱስ ሰው ! ይቺን የመሰለች ቆንጆ ሴት ውስጥ እያለች ነው እኔ ታላቁ የሮምና የአንጾኪያ ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ ብሴት እጦት የምብሰከሰከው ! ለምሆኑ ፈቃደኛ ሆናለች ?

ወታደር 2 ፡ ለሳምንት ቀጠሮ ይዘናል። ገና አላወቅነም

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ማወቅም ፈቃድ መጠየቅም ቀጠሮ መጠበቅም አያስፈልግም ! ሂዱና ጠፍራችሁ አምጡልኝ ! [ይወጣሉ]

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ አርሴማ መጣ ! በፊቴ ስትምነሸነሽ እንደ ፀሐይ ስታበራልኝ !እንደ ከዋክብት ድምቅ ድምቅምቅ ስትልልኝ ይታየኛል።

[መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት አስራ ሦስት

[መጋረጃ ሲከፈት ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ ወታደሩን በጥፊ እየጠፈጠፈ ይታያል]

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ተናገር የት ሄደች ? ተናገር አንተ የማትረባ

ወታደር 1 ፡ እዉነቴን ነው ጌታየ ከገዳማቸው ዉስጥ የሉም።

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ የሳምንት ቀጠሮ ይዛችሁ ይቺን ወርቅ ያስመለጣችሁኝ እናንተ ናችሁ ? ጋሌርየስ

ካህነ ጣኦት(ጋሌርዮስ) ፡ አቤት አለቃየ

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ሌሎች ወታደሮችን እዘዝና እነዚህን ደረመናም ምናምንቴዎች በመንኮራኩር ፈጭተው ስጋቸዉን ለሰማይ አሞራ ይበትኑልኝ ! እኔ ዲዮቅልጥያኖስ እኔ አግሪጳድ በቀል ከጀመርኩ ምንም ነገር ልቤን ሊያራራዉ አይችልም። ያችንም በመልኳ የኮራች ክርስቲያን ከገባችበት ጉበታችሁ አምጡልኝ።
ዲዮቅልጥያኖስ ላይ ብልጠት መሞከር ምን ያክል ዋጋ እንደሚያስከፍል አሳያታለሁ። አርሴማን አምጡልኝ ! አርሴማን አምጡልኝ

[መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት አስራ አራት

[መጋረጃ ሲከፈት እነ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ተቀምጠው ይታያሉ]

መነኩሲት 3 ፡ በዚህ በረሃ ተቀምጠን ረሃብ ፈጀንኮ ! ወደ ከተማ እንግባ ወይም ወደ ሌላ ቦታ እንሽሽ

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ወደ አርመን ከተማ ከገባን ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ እና የአርመኑ ንጉስ ድርጣድስ ስለሚተዋወቁ ስለኛ የነግራቸዋል። እያዛለን ! ወደ ከተማ የመሄዱን አሳብ እንርሳው !

ቅድስት አርሴማ ፡ በዚህ በረሃ ዉስጥ የሚላስ የሚቀመስ የለም። የያዝነው ስንቅም እያለቀ ነው። እባካችሁ እራሳችሁን አትርፉ። በእኔ ምክኛት ከዚህ በላይ ስትጎዱ ማየት አልችልም። ወደ ቦታችሁ ተመለሱ እኔ ብቻየን እሸሻለሁ።

አበምኔት ፡ አይሆንም ! ክርስቲያን ስለ ባልንጀራው ፍቅር እስከ ሞት ድረስ መታገል አለበት። ክርስትና እርስበርስ መዋደድ ነው። ባለንጀራህን እንደራስህ ዉደድ ይላል መጽሐፍ

ቅድስት አርሴማ ፤ የምትወዱኝ ከሆነ ! አሳቤን አክብሩልኝና ተመለሱ እኔ የምፈልገው ብቻየን መጋፈጥ ነው። በእኔ ምክንያት ስትጎዱ አለማየት ነው ምኞቴ ! ከወደዳችሁኝ ምኞቴን ፈጽሙልኝ !

አበምኔት ፡ አይሆንም አልኩሽ ! ጎርጎርዮስ ዝም አትበል እንጂ !

[ቅዱስ ጎርጎርዮስ ይነሳና ትንሽ ወደፊት ይራመዳል]

[ትንሽ ዝም ይልና]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አርሴማ ትክክል ናት ! በእርሷ ጉዳይ ሌላ ሰ ማስቸገር ጥሩ አይደለም።

መነኩሲት 2 ፡ ምን ?

መነኩሲት 1 ፡ ምን ማለትህ ነው ወንድማችን ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አወ ! በእርሱ ጉዳይ ሌላ ሰው መንገላታቱ ጥሩ አይደለም። ስህተት ነው።

አበምኔት ፡ ተው እንጂ ምን ሰይጣን ገባብህ ? ኧረ በስመ አብ በል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አልተሳሳትኩም ! እናንተ ያለአበሳችሁ በርሀብ ማለቅ የለባችሁም። ወደ ገዳማችን ተመለሱና ከእግዚአብሔር ጋር ኑሩ። የእስካሁኑ ይበቃችኋል። እኔ ግን ወንድሟ ስለሆንኩ ሥጋዬ ናት ! ያገባኛል። እኔ አብሪያት መከራዉን እቀበላለሁ። እናንተ ራሳችሁን አድኑ

አበምኔት ፡ በተሰቀለው ! በተሰቀለው ! እኛን ባዕድ አደረከን ! ሥጋዬ ናት ? እኛማ ባዕድ ነን ? እኛማ ባዕድ ነን

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡እንደሱ ለማለት ፈልጌ አይደለም አባቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ

አበምኔት ፡ አልክ እንጂ ! ለማለት ፈልገህ ነው እንጂ !

መነኩሲት 2 ፡ እኛንም እንደ እህቶችህ የምታየን ይመስለን ነበር። ለካ ተሳስተናል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ያለ አበሳችሁ በረሃብ አንጀታችሁ ሲታጠፍ ሳይ አሳዝናችሁኝ ነው።

አበምኔት ፡ በል ዝምበል ምን የሆነ ነው ይሄ !

መነኩሲት 1 ፡ ሁለተኛ እንዲህ ስትል ብንሰማ ልባችንን ትሰብረዋለህ።

መነኩሲት 3 ፡ ድጋሚ እንዲህ እንዳትል። እግዚአብሔር ይቅር ይበልህ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ እናንተም ይቅርታ አድርጉልኝ ! ይቅርታ አድርጉልኝ

አበምኔት ፡ በሉ አሁን እንጸልይ

አባታችን ሆይ _ _ _ _ _ _ _ _ _ _

[*መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት አስራ አምስት

[*መጋረጃ ሲከፈት ቅዱስ ጎርጎርዮስ እና አበምኔቱ ይታያሉ*]

አበምኔት ፡ እርግተኛ ነህ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ሌላ መፍትሄ የለም። እዚህ ቁጭ ብለን ረሃቡን አልቻልነውም። ስለዚህ ወደ ከተማ ሂጄ እየሰራሁ ገንዘብ በማግኘት እናንተን በድብቅ ለመርዳት አስቢያለሁ።

አበምኔት ፡ ብቻህን መሄድክን አልወደድኩትም እኔም አብሬህ ሄጄ ሥራ እቀጠራለሁ !

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አይሆንም እርስዎ ለእህቶቻችን ያስፈልጓቸዋል። በዛ ላይ ሽማግሌ ነዎት !

አበምኔት ፡ ስለ አንተ እስጋለሁ ልጄ ሌላ መፍትሔ የለም።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ በረሃቡ ጽናት የተነሳ ወደ ከተማ ለመሄድ እገደዳለሁ። ሌላ አማራጭ የለም።ጸሎተ ማርያም ይድገሙልኝ።

አበምኔት ፡ እግዚአብሔር ይጠብቅህ ! በምትሄድበት ሁሉ እመብርሃን ትከተልህ ! አቡነ ዘበሰማያት ጸሎተ እግዝእትነ [*መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት አስራ ስድስት

[*መጋረጃ ሲከፈት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከንጉሱ ወታደር ጋር ይገናኛል።*]

ወታደር 1 ፡ ና ወደዚህ ማን ነህ አንተ ? ከወዴት መጣህ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ባርነት መቀጠር ፊልጌ ነው ከሮም የመጣሁት።

ወታደር 1 ፡ እና ታዲያ ከሰው ሃገር ዘው ብሎ መግባት አለ። የያዝከዉን ቡትቶ አምጣ አስፈትሽ [ያየዋል] ለመሆኑ ምን ልሰራ ነው ያልከኝ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ባርነት ! ማንኛዉም አይነት ሥራ መስራት እችላለሁ።

ወታደር 1 ፡ ምግብ የማብሰል ችሎታ አለህ።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እችላለሁ። በደንብ እችላለሁ ።

ወታደር 1 ፡ እርግጠኛ ነህ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ በሚገባ ! ምግብ ለማብሰል የግድ ሴት መሆን አይጠበቅብኝም።

ወታደር 1 ፡ በጣም ጥሩ። ንጉሱ ድርጣድስ የአትክልት ስራ የሚሰራለትና ምግብ ቤቱን በኃላፊነት እየተቆጣጠረ የሚሰራለት ሰው ይፈልጋል። ከነ ዘር ማን ዘርህ ሰፍረህ የማትጨርሰው ደመወዝ ይሰጥሃል ! ትስማማለህ

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ንጉስ ድርጣድስ ?

ወታደር 1 ፡ አወ ድርጣድስ ምነው ደነገጥክ ችግር አለ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ኧረ የለም

ወታደር 1 ፡ በልና እንሂድ

[*መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት አስራ ሰባት

[*መጋረጃ ሲከፈት ንጉስ ድርጣድስ ምግብ እየቀመሰ ይታያል*]

[ቅዱስ ጎርጎዮስ ቆሟል]

ድርጣድስ ፡ እምም ! በጣም የሚጣፍጥ ምግብ ነው ያበላሃኝ ! አማልክቱ ይባርኩህ ! ለመሆኑ ከየት ነው የመጣህው ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ከሮም

ድርጣድስ ፡ *ሙያህን ወድጄዋለሁ* ! አተ ራስህ ነው የሰራሃው ወይስ ሴቶቹን አዘህ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እኔው ራሴ ነኝ ንጉስ ሆይ !

ድርጣድስ ፡ በጣም ጥሩ ጸባይ ካለህ ደመዎዝህ ይጨመራል። ብልጥ መሆን ብትሞክር ግን መፈጠርክን ነው የማስጠላህ ? ተግባባን

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ገብቶኛል ንጉስ ሆይ !

ድርጣድስ ፡ እኛ ወደ አደን ደርሰን እስከምንመጣ የምግብ ጠረንጴዛዉን ቤቱን አጽድትህ ጠብቀን ! የሚያግዝህ ሰው *መጥራት* ትችላለህ። [ይወጣሉ]

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ጌታ ሆይ ምን አይነት አጋጣሚ ነው። በጭካኔ ከዲዮቅልጥያኖስ ከማይተናነሰው ከድርጥድስ ቤት ልግባ ! ይህ የአንተ ፈቃድ መሆን አለበት። ከዚህ መሆኔ ለኔ አስቸጋሪ ቢሆንም አዲስ መረጃ በቅርብ ሆኖ ለመከታተል እና እህቶቼን ለመከላከል ጥሩ አጋጣሚ ነው። የአንተ ፈቃድ ይሁን ጌታዬ የአንተ ፈቃድ ይሁን !

[እየጸለየ *መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት አስራ ስምንት

[መጋረጃ ሲከፈት ንጉስ ዲዮቅልጥያኖስ ከጋሌርየስ ጋር]

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ ምን አርመኛ ?

ጋሌርየስ ፡ አወ ንጉስ ሆይ ወደ አርመኛ እንደሸሹ መረጃ ደርሶናል።

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ አርሴማን ካላገኘሁ መሞቴ ነው። አርሴማን ማግባት አለብኝ። አርሴማን ካላገባሁ እረፍት አይኖረኝም። ወደ ወዳጇ ወደ አርመኑ ንጉስ ድርጣድስ መለክት ላክበት። ማግባት የምፈልጋት ሴት በእርሱ ግዛት እንደተደበቀችና ጉሮሮዋን አንቆ ይዞ እንዲመልስልኝ ጻፍለት። ይህ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ትዕዛዝም እንደሆነ ንገረው

ጋሌርይስ ፡ ታዛዥ ነኝ 1 አሁኑኑ መልእክት እልክላሁ።

ዲዮቅልጥያኖስ ፡ አርሴማን ማግባት አለብኝ። (ይደጋግመዋል) አማልክቶ ኤ እርዱኝ አፖሎና አርጤምስ እባካችሁ የአፖሎና የአርጤምስ መንፈሶች ሃርዲሽ ማርኩስ አርሴማን አምጡልኝ !

[መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት አስራ ዘጠኝ

[መጋረጃ ሲከፈት ቅድስት አርሴማና ማህበሩ እየጸለዩ]

[ጎርጎርዮስ ጳድቅ ይደርሳል] [በችኮላ]

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ወገኖቼ !

በአንድ ላይ ፡ ወንድማችን !

አበምኔት ፡ እንዴት ነህ ልጄ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ እኔ ደህና ነኝ! እግዚአብሔር ይመስገን እናንተስ ?

ቅ አርሴማ ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት በሰላም አለን ! አረፍ በል !

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ አይ ጊዜ የለኝም። በግድ ነው ጊዜ አመቻቺቼ የመጣሁት ! ፊልግው ካጡኝ መጣራታቸው አይቀርም ! እንኩ ይሄ ጥቂት ምግብና ለወር የሚበቃ ገንዘብ ነው። ምግቡ ሲያልቅባችሁ አንዳችሁ ልሳችሁን ቀይራችሁ እየወጣችሁ ምግብ ግዙ ! እየተጠነቀቃችሁ ታዲያ በሉ እኔ ልሂድ

አበምኔት ፡ ኧረ ትንሽ ቆይ

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ጊዜ የለኝም አባቴ ይባርኩኝና ልሂድ ! [ይሄዳል]

ቅድስት አርሴማ ፡ አምላካችን ሆይ ወንድማችን ጠብቀው

አበምኔት ፡ ኃይለ አጋንንትን አድክምለት

መነኩሲት 1 ፡ ከድርጣድስ ከመጋለጥ ሰዉረው

መነኩሲት 2 ፡ እመቤታችን ሆይ በላባ ቤት ሳለ ለያዕቆብ ረዳቱ እንደነበርሽ ለወንድማችንም በድርጣድስ ቤት ረዳት ሁኝው

መንኩሲት 3 ፡ አሜን ! [እየጸለዩ መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ሃያ

አባት ፡ ጎርጎርዮስ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ ስሜን እኮ ጠሩኝ አብቴ እርስዎ ማን ነዎት

አባት ፡ አንንተ ከመወለድህ በፊት ጀምሮ በዚህ በረሃ የምኖር መናኝ ነኝ።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ይፍቱኝ አባቴ ይፍቱኝ

አባት ፡ የሠራሃው ኃጢአት በጢምህ ይድፋህ።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ምን አሉኝ አባቴ።

አባት ፡ በረከት እየባረኩህ ነው። ከፈጣሪ ታዝዣፎ አንተን ነው የምጠብቅዉ።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ እዉነት አባቴ ?

አባት ፡ አዎ ስለእህትህ እንስ ወገኖችህ መጨነቅን ትተህ ወደ ገዳም ተመለስና እኔን አገልግለኝ ተብለሃል። እነሱን እኔ እጠበቃቸዋለሁም ብሎሃል።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡[ያምታታል] ልሰናበታቸው ታዲያ ?

አባት ፡ ይህ መልእክት እንደደረሰህ ሳትዉል ሳታድር ሂድ ነው የተባልክ ! አሁኑኑ ወደ ገዳም ሂድ

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ጥሩበቃ ልጸልይና ልሂድ

አባት ፡ [እየተነሳ] እንደሰማህ ሳትዉል ሳታድር ነው የተባልክ ጸሎት አድርግ አልተባልክም።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ አይ ጸሎት አታድርግ የሚለግዚአብሔር የለም [እጁን ለጸሎት ይዘረጋል]

አባት ፡ ተው ተዉ ተዉ ይበናል (ሳይጣን ነበር)

ትዕይንት ሃያ አንድ

[መጋረጃ ሲከፈት ድርጣድስ እና ሰራዊቱ]

ድርጣድስ ፡ አይ ወዳጄ ዲዮቅልጥያኖስ ሴት ሴት ሴት መንሰፍሰፍ ! ይሄኔ እኮ እ=አንዲት የማትረባ ግሽጣ ራስ ትሆናለች ! ለመሆኑ የት እንዳለች ታዉቋል ?

ወታደር 2 ፡ በረሃ ዉስጥ ተደብቀው እንዳሉ ጥቆማ ደርሶናል።

ድርጣድስ ፡ እስቲ ሂዱና ይዛችሁ አምጧት ! ዲዮቅልጥያኖስ ልሙትልሽ ያላትን ሴትማ ማየት አለብኝ ! አይ ዲዮቅልጥያኖስ እንደዚህ ለሴት ይሸነፋል ! ና ማነህ እስቲ ጠጅ ቅዳልኝ !

ወታደር 2 ፡ ጎርጎርዮስ ስሁን የለም።

ድርጣድስ ፡ ምን ? የት አባቱ ሄደ ?

ወታደር 1 ፡ አናውቅም ንጉስ ሆይ !

ድርጣድስ ፡ ተጠገበ ማለት ነው። በሉ እናንተ ሂዱና አምጧት እኔ ራሴ እቀዳለሁ

[ይወጣሉ። ቀድቶ መጠጣት ይጀምራል። ጎርጎርዮስ ይመጣል]

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ይቅርታ ያድርጉልኝ ንጉስ ሆይ አረፈድኩ

ድርጣድስ ፡ ጥጋብ ተጀመረ። ድርጣድስ በትንሹ ሁሉ አይደነፋም። ከመጣብኝ ግን የጠገበ ልብህን አስተነፍስልሃለሁ።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ አይደገመኝም ንጉስ ሆይ ! ለመሆኑ ሰዎቹስ ?

ድርጣድስ ፡ አርሴማ የምትባል አንዲት የማትረባ ጥርሷን እያሳየች የንጉስ ዲዮቅልጥያኖስን ልብ ከበላች በኋላ ! ላግባሽ ሲላት በመልኳ ተመክታ እንዳንተ አይነቱን በግ ፊት አላገባም ብላ አርመንያ ዉስጥ ባለ በረሃ ተደብቃለች አሉ። እሷን ሊያመጡ ነው።

[ራሱን ይዞ ወይኔ ይላል]

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ያለችበት ታዉቋል አሁን ?

ድርጣድስ ፡ ቆይ ቆይ ከመቼ ወዲህ ነው ድርጣድስ ከተራ ባሪያ ጋር የሚያወራው ? እንደሚታጠብ ብርድ ልብስ ሳልጠቀልልህ ሂድና ምግብ አምጣልኝ

[በሃዘን እየወጣ መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ሃያ ሁለት

[መጋረጃ ሲከፈት ድርጣድስ ከሰራዊቱ ጋር። ጎርጎርዮስ ቅዱስ እያስተናገደ]

ድርጣድስ ፡ የወዳጄን ልብ ያሸነፈችዉን አርሴማን ላያት ነው። ዲዮቅልጥያኖስ እሷን ካላገባሁ ሞቼ እገኛለሁ ያለላትን ሴት እስኪ ልይለት ! እንደሷ አይነት ቆንጆ የለም ሲባል ነበር ! እናያለን አስገቢት !

[ቅዱስ ጎርጎርዮስ የሚደረገዉን ነገር በጥሞና ይከታተላል]

[ያስገቢትና ከፊቷ ያቆሟታል] [ዝም ብሎ እያያት ይቆማል] [ግራ ይጋባሉ]

ወታደር 1 ፡ ንጉስ ሆይ ችግር አለ ? [አይመልስም]

ወታደር 2 ፡ ንጉስ ድርጣድስ ! ንጉሳችን ! ኧረ ንጉስ ሆይ

ድርጣድስ ፡ አግቢኝ ! [ይንበረከካል] አግቢኝ አግቢኝና ገላግይኝ ! እንጋባና ንግስት አድርጌ ቤተ መንግስት ዉስጥ ላቀማጥልሽ [ታማትባለች]

ወታደር 2 ፡ ንጉስ ሆይ ! ረሱት እንዴት ዲዮቅልጥያኖስ እኮ ለራሱ ነው የፈለጋት ለእርሰዎ አይደለምኮ

ድርጣድስ ፡ ማነው ዲዮቅልጥያኖስ አላዉቀዉም።

ወታደር 1 ፡ ንጉስ ሆይ ይሄ ለእርሰዎ አደጋ አለው።

ድርጣድስ ፡ አደጋ ማነው ? አላዉቀዉም። መታገስ አልችልም አርሴማ። ይህን ቁንጅና አይቼ መታገስ አልችልም ጥያቄየን ተቀበይኝና ንግስቴ ሁኝ

ቅ አርሴማ ፡ “ እኔ የክርስቶስ ሙሽራ ነኝ። የማይሆን ነገር ነው። የመንግስተ ሰማያት ሙሽራ መሆን ይበልጥብኛል። ”

ድርጣድስ ፡ መንግስተ ሰማያት ? መንግስት ያልለው በዚህ ምድርኮ ነው። በሰማይ ፀሐይ ጨረቃ ከዋክብት ነውኮ ያለው ! ሰው በሰማይ አይኖርም ስለዚህ መንግስት የለም። እስኪ ቀና ብለሽ ሰማይን እይው ! ህይወት አይኖርምኮ ባዶ ነው። መንግስት ያለው በዚ አለም ነው። ከንቱ ቅዥትሽን ትተሽ ወደ እዉነተኛው ዓለም ብትመለሽ ይሻልሻል። የድርጣድስን መንግስት እያየሽው ነው። የሌለ ምናብ ፈጥረሽ መንግስተ ሰማያት ማለቱን ትተሽ እድልሽን ተጠቀሚበጥ

ቅ አርሴማ ፡ ያንተ መንግስት ኃላፊ ጠፊ ነው። የእግዚአብሔር መንግስት ግን ዘላለማዊ ነው። ብላሽ የሚሆን ኃላፊ ደስታ ከማያልፈው ዓለም ተድላና ደስታ ጋር ሲነጻጸር ኢምንት ነው። ይልቅ የኔን ምክር ስማኝ እንደ ጥላ ቶሎ ከሚያልፈው ምድራዊ ንግሳና ልብህን አንሳና የማያልፈዉን ዓለም ነገር እይ ! አስብ አመዛዝን ወደ አእምሮህ ተመለስ !

ድርጣድስ ፡ ጭራሽ ጭራሽ ትምህርት መስጠት ያምርሻል። ጸሚያለሽ እኔ ዉበትሽን አክብሬ በሰላም ብጠይቅሽ ብልጥ መሆን ፈለግሽ ! በጥፊ ብየ በጉልበት አንቺን ማግባት የሚያቅተኝ ይመስልሻል። ትእግስቴ ካልቀ ያልቅልሻል። ድርጣድስ ከተቆጣ ሰማይ ምድሩ አይበቃዉም።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ንጉስ ሆይ ይቺ ሴት እብድ ሳትሆን አትቀርም እርሷን ባታገባት ጥሩ ነው። ንጉስ ድርጣድስ ተራ ሴት ማግባት የለበትም። ልብሷን እየው እስኪ እንዴት እንደ ደከረተ ! እነዚህ ሰዎች ሰዉነታቸዉን ራሱ ታጥበው ራሱ የሚያዉቁ አይመስለኝም። ተራ ሴት አግብተህ ራስህን አታዋርድ። ታላቁ ንጉስ ይቺን ሴት አባራት ! ተዋት ትቅርብህ

ድርጣድስ ፡ ችግር የለዉም። ገላዋን ትታጠበዋለች። ልብስም ይቀየርላታል።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ እብደቷን ግን ማዳን አይቻልም። ንጉሱ እብድ አገባ ቢባል ሰዉ ምን ይላል ?

ድርጣድስ ፡ እብድ አይደለችም። በህይወቴ ሁሉ ክርስቲያኖችን ሳስፈጅ ነው የኖርኩት። መልሳቸውና ንግግራቸው እንዲህ ነው። አሳምሬ አውቃቸዋለሁ።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ግንኮ

ድርጣድስ ፡ በቃህ አንተን አማካሪ ያደረገህ ማነው ሂድ ቀጥል ወደ ስራህ። አንቺንም ለመጨረሻ ጊዜ ልጠይቅሽ ታገቢኛለሽ ወይስ አታገቢኝም ?

ቅድስት አርሴማ ፡ እግዚአብሔርን እሺ በሉት ዲያብሎስን ግን እንቢ በሉት

ድርጣድስ ፡ በጣም ጥሩ ! አሁን ድርጣድስ ጨካኝነቱን የሚያሳይበት ጊዜ ደርሷል። ወታደር

ወታደሮች ፡ አለን ንጉስ ሆይ

ድርጣድስ ፡ አብረዋት ያሉትን አስገቡልኝ [ያመጧቸዋል] ድርጣድስን ላሳይሽ ! ድርጣድስን ላሳይሽ ! እነዚህን ሰዎች በሰይፍ ቅሏቸው [ይገደላሉ። አርሴማ ታለቅሳለች] [ጎርጎርዮስ ፊቱን ዞሮ ያለቅሳል]

ቅ አርሴማ ፡ እህቶቼ ! እህቶቼ

ድርጣድስ እኔ እንደዚህ ነኝ ! ድርጣድስ ይሄ ነው አሁን ገባሽ ? ገባሽ ወይ ? የአበጠ ልብሽን አስተነፈስኩት ! ግና አፈነዳዋለሁ። [ማልቀስ ትቀጣላለች] አስከሬናቸዉን ዉሰድና ብዙ መሰሎቻቸዉን ከጨፈጨፍንበት ተራራ ጣለው ! አንቺም ነገ በሰው መሃል ታገቢኛለስሽ ! እምቢ ካልሽ የሚደርስብሽን አይተሻል። [ይወጣል]

ወታደሮች ፡ ድርጣድስ ታላቅ ነው / 4 /

[ቅዱስ ጎርጎርዮስ ይጠጋታል]

ቅ አርሴማ ፡ የእነሱ ይበቃል አንተንም እንዳይጨምሩህ ! በእኔ ምክንያት ወገኖቼን አስፈጀዋቸዉ እሺ በለኝና ከዚህ አካባቢ ጥፋ ! ስላንተ ማወቃቸው አይቀርም ቶሎ አምልጥ !

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ከሰማዕትነት ወዴት እሄዳለሁ ! ከእግዚአብሔር ወዴት እሄዳለሁ ? አልለይሽም ! [ወታደሩ ቀስ ብሎ ተጠግቶ ማድመጥ ይጀምራል]

ቅ አርሴማ ፡ አንተ ክርስቲያን መሆንክን የሚያዉቅ የለም። እባክህ ሂድ

ወታደር 2 ፡ ክርስቲያን ድሮም ጠርጥሬህ ነበረ ና ዉጣ [እያዳፋ ያወጣዋል]

ትዕይንት ሃያ ሦስት

[መጋረጃ ሲከፈት ድርጥድስ በንዴት እየተንጎራደደ]

ድርጣድስ ፡ ተዋረድኩ ተዋረድኩ ተፈርቼ ተከብሬ በኖርኩበት ሀገር ተዋረድኩ !ሴት እኔን ጠምዝዞ ጣለኝ ወይኔ ድርጥድስ ውይኔ ! ላግባሽ ባልኳት እጇን ጠምዝዛ ጥላ የሰው መሳቂያ አደረገችኝ። አሳፈረችኝ አፈርኩ ሰው መሀል አፈርኩ ! ድርጥድስ ታላቁን ሴት ጣለችው ያውም ሰው መሀል።

ወታደር 1 ፡ ይረጋጉ ጌታየ

ድርጥድስ ፡ አልረጋጋም እከካም ! በኔ ያደረገችው መቶ እጥፍ ሆኖ በሷ ላይ ይደርስባታል። ከፀሐይ በታች አለ በተባለ ስቃይ ሁሉ መፈጠሯን እስክትጠላ ነው መከራዋን የማበላት

ወታደር 2 ፡ ስቃዩን በምን እንጀምር ታዲያ ክቡርነተዎ !

ድርጣድስ ፡ በደንብ በጅራፍ ከገረፋችኋት በኋላ ዓይኗን አዉጡት ! ከዛ ጡቷን ቁረጡት ሰዉነቷ ከተመላለጠ በኋላ የሚያቃጥል ነገር ነስንሱባት ! መጨረሻዉን አብረን እናያለን። ለአማልክቶቻችን የማጸግድ ከሆነ አንገቷን በሰይፍ ቁረጡት

ወታደር 1 ፡ የወንድሟን የጎርጎርዮስን ነገር ምን እናድርገው

ድርጣድስ ፡ የሷን መጨረሻ ካየን በኋላ ወደሱ ቅጣት እንመጣለን። እስከዛ እስር ቤት ዉስጥ ይቆይ ! አሁኑኑ ሂዱና ዓይኗን አውጡት ጡቷን ቁረጡት

ትዕይንት ሃያ አራት

[መጋረጃ ሲከፈት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከድርጥድስ ፊት ታስሮ ቆመ]

ድርጣድስ ፡ ከታላቁ ድርጣድስ ፊት ሁሉ ነገር እንደስጦ የተሰጣ መሆኑ አልገባህም ነበር። ክርስቲያን በዛ ላይ የአርሴማ ትልቅ ወንድም መሆንህን ደብቀህ ቤተ መንግስት ዉስጥ ባርነት ተቀጠርክ። ድፍረትህን ወድጀዋለሁ። ሆኖም እንዳንተ አይነቱ ቡትቷም ቀርቶ አለት ዉስጥ ያለች ትል እንኳን አትሰወርም። ጸራልኝ ስለነበረው ጣፋጭ ምግብ ስል ይቅርታ ላደርግልህ እወዳለሁ። አምላክ የምትለውን የተሰቀለ ሰዉየ ተዉና አማልክቱን አምልክ ልክ እንደከዚህ ቀደሙ ምግብቤቱን ተቆጣጠር። ባለሟሌ አደርግሃለው።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ሙሴም ከግብጽ ብዙ ባለጠግነት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ መሆኑን አየ

ድርጣድስ ፡ ምን ? ሙሴ ? ያንተን ሙሴ እዛ ጣልና የተሰጠህን እድል ተጠቀምበት

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ይልቅ አንተን ልምከርህ በሞት ሳትወሰድ በእዉነተኛው አምላክ እመን

ድርጣድስ ፡ እኮ አንተ እኔን ልትመክረኝ ወገኖችህን ታሪክ እንዳደረኳቸው ረሳሃው ? ድርጥድስ ከተናደደ የአበጠ ልብ ያስተነፍሳል ያፈነዳል

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ አቤቱ አምላኬ ሆይ ! የልቦናቸዉና ዓይን አብራላቸው። ብርሃን አንተን ለማየት አብቃቸው። ጌታዬ ሆይ እነዚህን ሰዎች ሳልሞት ክርድቲያን አድርግፊህ እንድታሳየኝ እለምንሃለሁ !

ድርጥድስ ፡ ዉሰዱና ይህን ኮስማና ያበጠ ልቡን አፈንዱለት

ወታደር 1 ፡ ምን እናድርገው ንጉስ ሆይ ?

ድርጣድስ ፡ ቆዳው ተልጦ አጥንቱ እስኪታይ ግረፉት። በእሳት አቃጥሉት ፤ በመዶሻ ቀጥቅጡት አቋሙን የማይቀይር ከሆነ የማደርገዉን አውቃለሁ። አሁኑኑ ዉሰዱት (ያወጡታል) ክርስቲያን አድርገህ አሳየኝ ኧረ ይሄ ጎስቋላ

ትዕይንት ሃያ አምስት

[መጋረጃ ሲከፈት ድርጣድስና ወታደሮቹ]

ድርጣድስ ፡ አሁንም አቋሙን አልቀየረም ? በጣም ጥሩ ከነህይወቱ መጸዳጃ ቤት ዉስጥ ወርውሩት ! በፍጥነት ! እዛው ሽቶ ይሙት ድርጣድስ ነኝኮ

[*መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት ሃያ ስድስት

ከ 15 ዓመት በኋላ

[*መጋረጃ ሲከፈት ድርጥድስ እና ወታደሮቹ*]

ድርጣድስ ፡ ዛሬ ምን አይነት ቀን ነው ? የሚታደን አዉሬ እንዴት ይጠፋል

ወታደር 1 ፡ ንጉስ ሆይ ካልሆነ ከዚህ ጥላው ላይ አርፈን እንጠብቅ (ከቆይታ በኋላ እርኩስ መንፈስ መጥቶ ይዳስሰዋል)

ድርጣድስ ፡ ፊቴን አቃጠለኝሳ ! ኧረ አሳከከኝ (ፊቱን ያካል)

ወታደር 2 ፡ ምን ተፈጠረ ንጉሳችን

ድርጣድስ ፡ ሰዉነቴን አንገበገበኝ

ወታደር 1 ፡ የአማልክት ያለሽ ! ንጉሳችን ፊትዎትኮ እየተቀየረ ነው።

ወታደር 2 ፡ ኧረ ማከከዎን ያቁሙ ፊተዎን በጭቀው ሊጥሉት እኮ ነው። ኧረ አርጤምስ ፊታቸው እዉነትም እየተለወጠ ነው። ንጉሳችን ንጉሳችን (ወታደሩንም ይዳብሰዋል)

ወታደር 1 ፡ ኧረ እኔንም አንገበገበኝ

ወታደር 2 ፡ ምን ? ወይኔ ጉዴ ምን አይነት ቀን ነው ? ወይኔ ጉዴ ወይኔ እናቴ

ወታደር 1 ፡ አቃጠለኝ ! *መላ ሠዉነቴን አንገበገበኝ መንፈስ መሆን አለበት*

ወታደር 2 ፡ ምን ? *መንፈስ* ? አሁን መሮጥ (በጥፊ ይዘርረዋል)

[*መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት ሃያ ሰባት

[*መጋረጃ ሲከፈት የድርጣድስ እህት እያለቀሰች*]

እህት ፡ ወይኔ ወንድሜ / 4 / ወደ አዉሬነት ተቀይሮ ይቅር ! ወይኔ !

መልአክ ፡ አንቺ ሴት አታልቅሽ ወንድምሽን መፈወስ የሚችለዉን ሰው እኔ እነግርሻለሁ ባሮጌው ቆሻሻ ቤት ዉስጥ ከነህይወቱ የተቀበረ ጎርጎርዮስ የሚባል ቅዱስ ሰው አለ። በእግዚአብሔር ቸርነት አሁንም በህይወት አለ። እሱን አስወጪና ወንድምሽ ይፈወሳል

እህት ፡ ጌታዬ ሆይ አንተ ማን ነህ

መልአክ ፡ እነ ሰማይና ምድርን የፈጠረ የእዉነትኛው አምላክ የእግዚአብሔር መልአክ ነኝ

እህት ፡ እዉነተኛው አምላክ ወይ ምስጋና ላንተ ይገባል (እየደጋገመች)

[*መጋረጃ ይዘጋል*]

ትዕይንት ሃያ ስምንት

[*መጋረጃ ሲከፈት የድርጣድስ እህት ከቅዱስ ጎርጎርዮስ ስር ተደፍታ*]

እህት ፡ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ይቅር በለን ! ያደረግንብህን ሁሉ ይቅር በለን

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ሁላችንም የእግዚአብሔር ምህረት የሚያስፈልገን በደለኞች ነን። ተነሽ ልጄ እባክሽን (ያነሳታል) ለመሆኑ ወንድምሽ እና ባለሟሎቹ የት ናቸው

እህት ፡ እዛው በረሃው ዉስጥ ናቸው። ፈቃደኛ ከሆንክ አሁን መሂኦእድ እንችላለን።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ጌታ ሆይ በምህረትህ ጎብኛቸው

ትዕይንት ሃያ ዘጠኝ

[*መጋረጃ ሲከፈት እነድርጣድስ እርያ ሆነው ይታያሉ*]

[ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከድርጣድስ እህት ጋር ይገባል]

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ጌታዬ ሆይ ኃይል ያንተ ነው። እኒህን ባርያወችህን ፈዉሳቸው (በመስቀል ምልክት ያማትባል) ይፈወሳሉ። አይዟችሁ አትፍሩ

ድርጣድስ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እዉነተኛ አምላክ ነው።

ወታደሮች ፡ በቅድስት ስላሴ እናምናለን። ጌታ ሆይ ተመስገን ! እናመሰግንሃለን ቸሩ አምልካ ሆይ !

ድርጣድስ ፡ ምስጋና ላንተ ይገባል።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ተመስገን አምላኬ ጸሎቴን ሲለሰማሃኝ ከመሞቴ በፊት እነዚህን ልጆቺህን ክርስቲያኖች አድርገህ ስላሳየሀኝ ተመስገን ተመስገን

ድርጣድስ ፡ ከዚህ በኋላ በአርመንያን ግዛት ዉስጥ በክርስቶስ የማያምን ሰው ካለ ዝቅ ብለህ ባቱን ከፍ ብለህ አንገቱን በጥስልኝ

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ተው ልጄ ! እግዚአብሔር ሰው ወዶ እንዲያምንበት ይፈልጋል። በጉልበትማ ቢሆን ግርማውን ገልጾ ሁሉን ማሳመን ይችል አልነበር ? በዛ ላይ ክርስትና የበደሉንን ይቅር እንድንል ታዘናለች እንጅ በቀልን አታስተምርም።

ወታደር 1 ፡ አባታችን የሃይማኖትን ትምህርት አስተምረን ? (ይቀመጣሉ)

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሁሉ ቀድሞ የነበረ ነው። በቦታ አይወሰንም ! ጊዜ አይሰፈርለትም ! በእግዚብሔር ዘንድ ትላንት ነገ ዛሬ የለም። አኗኗሩ የማይመረመር ድንቅ ነው። በባህርይው ሞት በመንግስቱ ሽረት የለበትም። እንዲህ ሆኖ ሳለ ክብሩ በባህርይው እንደቀረ አይቶ ክብሩን እንዲወርሱ ስሙን እንዲቀድሱ ፍጥረታትን ፈጠረ። ገና ሳንፈጠር ነው የወደደን ልጆቹ።

[እያስተማራቸው መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ሠላሳ

[መጋረጃ ሲከፈት ቅዱስ ጎርጎርዮስ በመንበሩ ተቀምጦ ከድርጣድስ ጋር እያወራ]

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ እና የጎደለ ነገር አለ ?

ድርጣድስ ፡ እግዚአብሔር ይመስገን በእርሰዎ ጸሎት ሁሉም ነገር ሙሉ ነው።

ቅ ጎርጎርዮስ ፡ እሷን ስድብ ተው አላልኩህም ? በቀጣዩ ክብረ በዓል ዲያቆናትንና ካህናትን ስለምንሾም የቤተክርስቲያንን ትምህርት የተማሩትን እንዲዘጋጁ ንገራቸው። (መልእክት ይመጣለታል ፤ ያነበዋል ፤ መሄድ ይጀምራል)

ድርጣድስ ፡ አባታችን ወዴት ትሄዳለህ ?

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ፡ አርዮስን ለማውገዝ

[ይወጣል። መጋረጃ ይዘጋል]

ትዕይንት ሠላሳ አንድ

[መጋረጃ ሲከፈት ቄስ ማሩ ሰለሞንና አስቴር]

ቄስ ማሩ ፡ ከዛ በኋላ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ሃይማኖትን ካረቀቁ 318 ሊቃዉንት አንዱ ሆነ። እስካረፈበት ቀን ድረስ የእረኝነት ስራዉን በሚገባ ሰራ። እረፍቱ ሰኔ 15 ቀን ሲሆን መስከረም 19 ቀን ከተቀበረበት መጸዳጃ ቤት የወጣበት ነው። በረከቱ ይደርብን።

ሰሎሞን ፡ የቅዱሱ ታሪክ ራሴን እንድወቅስ አድርጎኛል።

አስቴር ፡ እግዚአብሔር ይቅር ይበለን እንጂ የኛ በደል ብዙ ነው።

ሰሎሞን ፡ የአስራት ብር ክፈሉ ፣ ቁረቡ ፣ ንስሐ ግቡ ሲሉን እየተጋፉኝና እያስገደዱኝ ይመስለኝ ነበር። ሰማዕታቱ ያንሁሉ ስቃይ የተቀበሉት ለነፍሳቸው ሲሉ በፈቃዳቸው መሆኑን ስረዳ ግን ሁሉም ነገር ለኔ ጥቅም መሆኑ ለራሴ መሆኑን ተረድቻለሁ። ይቅር በለኝ ፈጣሪ !

ቄስ ማሩ ፡ ጎሽ እንዲያ ነው። ኑዛዜያችሁን ከመቀበሌ በፊት አንተን ብቻህን ላናግርህ ፈልጌ ነበር።

(አስቴር ትወጣለች)

ሰሎሞን ፡ ምን ድን ነው አባቴ ?

ቄስ ማሩ ፡ ምስጢር ትጠብቃለህ ? የምትችል ከሆነ አንድ ነገር ላዉጋህ ?

ሰሎሞን ፡ ኧረ አልናገርም አባቴ

ቄስ ማሩ ፡ እንደነገርኩህ ከእግዚአብሔር የሆነዉንና ምትሀቱን መለየት የሚችሉ ፍጹማን ናቸው።
እዉነተኝም ሆነ አልሆነ የቅዱሱን ታሪክ እንድታውቅና ለንስሐ አብቅቶሃል። ዋናው ነገር ይሄ ነው።

ሰሎሞን ፡ አወ አባቴ ዋናው ነገር እኔ ንስሐ መግባቴ ነው። ታዲያ ምስጢሩ ምንድን ነው ?

ቄስ ማሩ ፡ ምስጢሩማ ! ከዚህ አካባቢ ራሳቸዉን ደብቀው አልባሌ መስለው የሚኖሩ ፍጹም አሉ።

ሰሎሞን ፡ እዉነት ? የበቁ አባት አሉ ?

ቄስ ማሩ ፡ ተረጋጋ እንጂ እንግዲህ እናንተ ደግሞ ችግራችሁ ይሄ ነው። ቀስ በል እንጂ

ሰሎሞን ፡ እሽ አባቴ እሽ

ቄስ ማሩ ፡ እኔ ስለማዉቃቸው ያየሀዉን ራዕይ ከእግዚአብሔር ይሁን ከሳይጣን ሊነግሩን ይችላሉ።
በረከታቸዉን እንድትቀበል ነው እንጂ ማወቁ አስፈላጊ አይደለም። ግን አደራ ለሰው አትንገር

ሰሎሞን ፡ ምንም ችግር የለዉም አባቴ

ቄስ ማሩ ፡ በል ደርሰን እንምጣ (መሄድ እየጀምሩ) ከረፈደም ቢሆን ያንተ ልብ መግዛት ደስ ብሎኛል። ልክ
በአስራ አንድ ሰዓት ወደ አትክልት ቦታ ሂዶ እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ሰርቶ ዋጋ እንዳገኘው ሰዉየ ነው
የመሰልከኝ (ሰሎሞን ይቆማል ፤ ያስባል)

ሰሎሞን ፡ እንዴ እንዴ

ቄስ ማሩ ፡ ምን ሆነሃል ?

ሰሎሞን ፡ ልሞት ነው ልሞት ነው ልሞት ነው ቄስ ማሩ

ቄስ ማሩ ፡ ምንድን ነው ነገሩ ? አሁን ደና አልነበርክ ምን ተፈጠረ ?

ሰሎሞን ፡ ትርጉሙ ምንድን ነው ?

ቄስ ማሩ ፡ የምኑ ?

ሰሎሞን ፡ የ አስራ አንድ ሰዓት

ቄስ ማሩ ፡ እ ! እሱን ነው እንዴት ምሳሌዉን እንደምታዉቀው ከአትክልት ቦታው አንዱ በሦስት ሰዓት አንዱ
በስድስት ሰዓት አንዱ በዘጠኝ ሰዓት ተቀጥረው ሲሰሩ ባለቤቱ አስራ አንድ ሰዓት ስራ ፈቶ ይቆመ አንድ ሰው
አግኝቶ ስራ ፈተህ ለምን ቆምክ ወደ አትክልት ቦታየ ሂድና ስራ ብሎ ቀጠረው በአስራ ሁለት ሰዓት ዋጋ

ሲሰጥ ከሁሉም ጋር እኩል ከፈለው። ነገር ላለማብዛት በሦስት ሰዓት የተባለ ህጻንነት ስድስት ስዓት የተባለ ወጣትነት በዘጠኝ ሰአት የተባለ ጎልማሳነት በአስራ አንድ ሰአት ከረፈደ የመጣው የሽምግልና ምሳሌ ነው። አስራ ሁለት ሰአት ደግሞ የሞት ጊዜ ነው።

ሰሎሞን ፡ እኮ በቅርቡ ልሞት ነው። ወይኔ ገና ንስሐየን ሳልጨርስ

ቄስ ማሩ ፡ የምን መአት ነው ምታወራው ማነው ትሞታለህ ያለው

ሰሎሞን ፡ ሰክሬ ነበር በደንብ ትዝ አይለኝም እብድ ነገር ነው መስለኝ ስንት ሰዓት ነው ብሎ ጠየቀኝ ሰዓቴን ሳየው አስር ጉዳይ ለ አስራ ሁለት ነበር ተሎ በል ልጄ ረፍዶብሃል አለኝ። ከዛ አሹፈበት ሄድኩ

ቄስ ማሩ ፡ እና ?

ሰሎሞን ፡ እናማ ልሞት ነው !

ቄስ ማሩ ፡ ምን ነክቶሃል በአስራ ሁለት ሰዓት ከሆነ መሽቶብሃል ያለህ እዉነቱን ነው። በዚህ ባልታመነው ጊዜ ወደ ቤት መግባት ጥሩ ነው።

ሰሎሞን ፡ አይደለም አይደለም አስር ጉዳይ ለአስራ ሁለት መሆኑን እያወቀ ነው የጠየቀኝ። አስራ ሁለት ሰዓት የሚገልጸው የመሞቻ ጊዜን ከሆነ ! አስር ጉዳይ ለአስራ ሁለት ማለት ኧረ ጉድ ኧረ ጉድ ! አልቋል አልቋል ! አልቋል ቄስ ማሩ መሞቴ ነው።

ቄስ ማሩ ፡ መስሎህ ነው ልጄ ሳይጣን ነገሮችን እያቀነባበረ ነው። ጊዜየ አልቋል አልደርስም እንድትል አውቆ ተስፋ ሊያስቆርጥህ ነው። ተረጋጋ ልጄ ና መስቀል ተሳለም ጻ ርኩስ መንፈስ ሩቅ ዉዱቅ አቡነ ዘበሰማያት እየደገምን እንሂድ አትመነው ልጄ ይህን መናጢ ዉሸታም።(አቡነ ዘበሰማያት እያሉ ይሄዳሉ)

ትዕይንት ሠላሳ ሁለት

[መጋረጃ ሲከፈት ቄስ ማሩና ሰሎሞን ቆመው ይታያሉ]

ቄስ ማሩ ፡ አባታችን እኔ ነኝ ደህና ዋሉ ? (ለማኙ ይወጣል)

ሰሎሞን ፡ እንዴ እንዴ ለማኙ ራሱ ነው ራሳቸው ናቸው ሰዓት የጠየቁኝ ቅዱስ አባቴ (ሮጦ ይሰግድላቸዋል)

ለማኝ አባት ፡ ቅዱስ ? ኧረ እኔ ለማኝ ነኝ። ተነስ ልጄ በኪዳነ ምህረት በል ተነስ ቅዱስ ወይ ጉድ አታሰማኝ የለህ።

ቄስ ማሩ ፡ በረከትዎትን እንዲቀበል ነው ያመጣሁት

ለማኝ አባት ፡ እኔ ነኝ በረከት የሚያስፈልገኝ አንድ ነገር ልንገራችሁ እኔ ፍጹም ስይደለሁም ተሳስታችኋል። ፍጻሜዉን ሳታይ ሰዉን አታመስግነው ብሏል ሲራክ ያልሞተ ሰው ቁርጡ አይታወቅም

ሰሎሞን ፡ ይምከሩኝ አባቴ (ወደ ቄስ ማሩ ብቻችንን ይተዉን በሚል ዕይታ ያያሉ)

ቄስ ማሩ ፡ በሉ ተጫወቱ እኔ በዚሁ ደብሩን ተሳልሜው ልምጣ

ለማኙ አባት ፡ ባለቤትህ ላንተ ትበቃለች። ምን አሳጣችህ ?

ሰሎሞን ፡ ሙያዋ በጊዜ ይስተካከላል ብየ ታገስኩ ጸባይዋ ግን ከአቅሜ በላይ ሆነ

ለማኙ አባት ፡ እርሷ ላንተ መስቀልህ ናት ተሸከማት ለመሆኑ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ከተቀበለው መከራ መስቀል እና ካንተ ሚአት ጸባይ የማን ይከብዳል

ሰሎሞን ፡ ኧረ ምን አገናኝቶት አባቴ የኔ ሚስት ምን አላት

ለማኝ አባት ፡ እንግዲያዉስ ቻላት በዛው ለመሆኑ ለምንድን ነው ንስሐ የማትገባው ?

ሰሎሞን ፡ በዋናነት ጊዜ ስለማጣ ነው። ስራ እየበዛብኝ

ለማኝ አባት ፡ አሞህ ያዉቃል ልጄ

ሰሎሞን ፡ አው እንደዉም በቅርቡ በጣም አሞኝ ነበር።

ለማኝ አባት ፡ እና ምን አደርግክ ልጄ ?

ሰሎሞን ፡ ለሁለት ሳምንት ስራ አቋርጬ ታከምኩ

ለማኙ አባት ፡ ኃጢአትምኮ በሽታ ነው ልጄ። ስጋዊ ደዌ አሞህ ስራህን ሁሉን ነገር ትተህ ልትታከምክ ሄድክ ነፍስህ በኃጢአት ደዌ ተይዛ ግን ለማሳከም ጊዜ አጣህ። ቁረብ ሲሉህ ለምንድን ነው ምታፈገፍገው ? (ዝም ይላል) የዘላለም ህይወት የሚሆንህን ቅዱስ ስጋና ክቡር ደም ታፈገፍጋለህ ጊዚያዊና ቆሻሻ ወደ መሆን የሚለወጠዉን ምግብ ግን በደንብ ካልተሰራልኝ ብለህ አንባጓሮ ታነሳለህ። ያንተን ሰዉነት ቆርጠህ ስጠኝ አላለህ ? የኔን ስጋና ደም እንካና ከኃጢአትህ ታጠብኮ ነው ያለህ ህይወትን ልስጥህ ብሎ ከሸሸህው አንድ ነገር ስጠኝ ቢልህ ምን ልትል ነው። ለመሆኑ ትጾማለህ

ሰሎሞን ፡ እስካሁን አልጾምም

ለማኙ አባት ፡ ለምን

ሰሎሞን ፡ እግዚአብሔር ችግር የለበትም ብየ

ለማኙ አባት ፡ አማክረህዋል (ሰሎሞን መልስ ያጣል) በል ልጄ እንግዲህ ልብ ግዛ እንደ ሰማዕታቱ ያንን ያዕክል መከራ አልመጣብህ። አስራት መክፈል ፤ ንስሐ መግባትና መቁረብ ይቀትህ ?

ሰሎሞን ፡ ልክ ነዎት አባቴ ይቅር ይበለኝ እንጂ ሁሉንም ነገር ማድረግ እየቻልኩ ነበር። ከባድ መከራ ሳይመጣብኝ ነው ሳሾፍ የኖርኩት እኒያ ነገስታት ግን ሰማዕታቱን ከባድ ግፍ አድርሰውባቸዋል። እግዚአብሔርን ተቃዉመዉታል አሳደዉታል።

ለማኙ አባት ፡ አንተም እኮ አንዱ አሳዳጁ ነህ ልጄ

ሰሎሞን ፡ እኔ ?

ለማኙ አባት ፡ አወ ልጄ አህዛብ ልጆቹን እያረዱ ቤተክርስቲያኑን እይቃጠሉ እንዳሳደዱት የሱ ማደሪያ የሆነ ሰዉነትክን በዝሙት እያቃጠልክ የምታሳድደው አንተ ነህ። (አዝኖ ይቀራል) በል ሂድ አላብዛብህ ከሰማዕታቱም ተማር ፤ አስራቱን አዉጣ ፤ ጹም ጸልይ ህጉን ጠብቅ ፤ ንስሐ ግባ ፤ ቁረብ በል ሂድ።

ሰሎሞን ፡ ጸሎት ያድርጉልኝ አባቴ (ጸሎት እየተቀበለ መጋረጃው ይዘጋል)

ተፈጸመ !!!